የኢትዮጵያ ታሪክና የወደፊት **የትግል አቅጣጫ ...**

ገጽ 14

የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት እንዴት?

ገጽ 8

## አኬልዳማዋ ኢትዮጵያ



ገጽ 11


# ባልደራስ

1ኛ ዓመት ቁጥር 03 ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም.


# ሁለት መቶ አማራዎች



# በወለጋ ተረሸኑ

## የሳተናው ሊቀመንበር ሲሳይ አየለ ላይ ተከፈተው ዶሴ በዳኞች መካከል ግጭት ፈጠረ

ገጽ 3

## ከአሥራት ወልደየስ አንደበት

ገጽ 16

# ተከታታዩ ማንነት ተኮር ጥቃት በህዝቡ ቆራጥ ትግል ሊመከት ይገባል!

ባለፉት ሁለት ዓመታት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ላይ የብሔር ተኮር ጅምላ ጭፍጨፋዎች እየተፈፀሙ ናቸው፡፡ እነኝህ ጭፍጨፋዎች በልዩ ልዩ የኦሮሚያ ‹ክልል› አካባቢዎች፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ጉራፋርዳ፣ በቤንሻንጉል እና በሌሎችም አካባቢዎች በሚኖሩ የአማራ ተወላጆች ላይ የተፈፀሙ ሲሆን ‹ነፍጠኛ› በሚል መለያ ተግባራዊ የተደረጉ ናቸው፡፡ በቅርቡ ደግሞ በአፋርና በሶማሌ ክልል በኢትዮጵያውያን መካከል በተነሳ ግጭት ሀያ ሰባት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን አንደወጡ ቀርተዋል። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ግጭትና የጅምላ ሞት የተለመደ ወንጀል ሆኗል። በማንነት ላይ ያተኮረ  ግጭት ከመነሳቱ በፊት ምልክቶችን እያጠና ለመከላከል የሚችል መንግስት የለንም። የዘር ግጭት ምልክቶች አድገው ግጭትን ሲፈጥሩ ግጭቶችን በፍጥነት የሚያስቆም መንግስት የለንም። ግጭቶች ከተፈጠሩ በኋላ ወንጀለኞችን ተከታትሎ ለፍርድ የሚያቀርብ መንግስት የለንም። እንዴውም በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት የግጭቱ ዋና ተዋንያን ሆነው ይታያሉ።  የህዝባችን ደህንነት አደጋ ላይ የወደቀው በዚህ ምክንያት ነው።

ባለፉት ሁለት አመታት ዶክተር አብይ ብሄራዊ መግባባት ለማምጣት ካለመቻሉም በላይ ሀገሪቱ በከባድ መፈናቀልና የዘር ግጭት መከራ ውስጥ እንድታልፍ ተደርጋች። በጌዲኦ በጉራጌ በኦሮሞ በትግራይ በቡርጂ በአማራ ወገኖቻችነ ላይ በዞር ጥቃት ተፈፅሟል ። አሁንም ቀጥሏል። ሀይ የሚል የለም። ይህንን መግለጫ ስናዘጋጅ በምእራብ ወለጋ ጊምቢ ውስጥ በመቶ የሚቆጠሩ አማሮች መገደላቸውን እየሰማን ነው። በተለይ በአማሮች ላይ እየደረሰ ባለው እልቂት የዶክተር አብይ መንግሥት ተጠያቂ ነው።  የኢትዮጵያ ህዝብ በብሄር በሀይማኖት ሳይከፋፈል ለጋራ ሰላሙ መታገል አለበት። የህዝቡን ደህንነት የሚያስጠብቅ መንግሥት በሌለበት ሀገር ህዝቡ ራሱን በራሱ መጠበቅ አለበት። አማሮች ተለይተው በማንነታቸው ሲጠቁና ሲገደሉ በፍጥነት ተደራጅተው መመከት አለባቸው።

**ባልደራስ ጋዜጣ**
መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም.
ተመሰረተ

በየ15 ቀኑ የሚታተም

**አሳታሚ**
ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ
ፓርቲ (ባልደራስ)

**ዋና አዘጋጅ**
ጌጥዬ ያለው
ክፍለ ከተማ፡- ቂርቆስ
ወረዳ፡- 02 የቤት ቁጥር፡- አዲስ
ስልክ፡- +2519 24 51 70 77
ኢ-ሜይል፡- newsgett@gmail.com

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ወግደረስ ጤናው

**አምደኞች**
ገለታው ዘለቀ
ኢንጂነር ጌታነህ ባልቻ

**አርታዒ**
መሰበወርቅ ቅጣው
ነብዩ ውብሸት

**ፀሐፊ፡-** ሕይወት ዳዊት

**የገፆች ቅንብር** ሐብ-ዲዛይን

**ገፀ ድር አስተዳደር** ኢስያስ ፅጉ

# ሁለት መቶ አማራዎች በወለጋ ተረሸኑ





በኦሮሚያ ‹ክልል› ግንቢ ዞን ጉሊሶ ወረዳ ጋዋ ቃናቱ ቀበሌ ይኖሩ የነበሩ አማራዎች እሁድ ጥቅምት 22 ቀን 2013 ዓ.ም. በታጣቂዎች ተረሽነዋል። የረሸናቸው የኦነግ ታጣቂ ቡድን ሲሆን ድርጊቱን ከመንግሥት መዋቅር ጋር በትብብር እንደፈፀሙትም ከሞት የተረፉ የአይን እማኞች ገልፀዋል። የሟቾችን ቁጥር በትክክል ለመግለፅ መንግሥት መረጃ እያጠናቀረ እንደሆነ የገለፀ ሲሆን ከአካባቢው እየወጡ ያሉ መረጃዎች ግን ከሁለት መቶ በላይ እንደሚጠጉ ይገልፃሉ። ነዋሪዎችን ለስብሰባ ከጠሩ በኋላ በተሰበሰቡበት ነው በጠመንጃ ተኩሰው የረሸኗቸው።

ጅምላ ጨፍጫፊው ቡድን ከ50 እስከ 60 የሚደርሱ የሰራዊት አባላት እንዳሉትም እማኞች ተናግረዋል። ይህንን ጭፍጨፋ ጨምሮ በተከታታይ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች እየተፈፀመ ላለው አማራን የማፅዳት ዘመቻ የወንጀሉን ሙሉ ሓላፊነት የአብይ አህመድ መንግሥት መውሰድ እንዳለበትም የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) በመግለጫው አስታውቋል። «በአገሪቱ ውስጥ ለበርካታ አስርት አመታት በአማራ ሕዝብ ላይ ማንነትን መሰረት ያደረገ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈፅሟል። እየተፈፀመም ይገኛል። ጥቃቶቹ ሲደርሱ እንደሚችሉ በተደጋጋሚ የያሳወቅን ቢሆንም ተጨባጭ መፍትሔ ሊገኝ አልቻለም።» ብሏል አብን በመግለጫው።

«እየተፈፀመ ላለው የዘር ማጥፋት ወንጀል ኦሕዴድ መራሹ ብልፅግና ግንባር ቀደም ተጠያቂ ነው» ሲል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በመግለጫው አስታውቋል። «በአማራ ሕዝብ ላይ የሚፈፀመው የዘር ማጥፋት ወንጀል ተባብሶ ቀጥሏል። መንግሥትም በአማራ ሕዝብ ላይ የሚፈፀመውን ተደጋጋሚ የዘር ማጥፋት ወንጀል በስሙ ከመጥራትና ብሔራዊ የደህንነት ስጋት አድርጎ ጥቃቱን ከማስቆምና የችግሩን ፈጣሪዎች በቅጡ ለይቶ የሚመጥን ርምጃ በወቅቱ ከመውሰድና የሕዝቡን ደህንነት ከመጠበቅ ይልቅ እሹሩሩ በማለትና ወንጀሉን በማድበስበስ የወንጀሉ ቀንደኛ ተባባሪ ሆኖ ይገኛል።» ብሏል መኢአድ።

ገዥው ፓርቲና መንግሥት ጅምላ ጭፍጨፋው እንደተፈፀመ ያመኑ ቢሆንም በጥቅሉ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰ ጥቃት አድርገው ከማቅረብ በስተቀር በአማራ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ መሆኑን አልገለፁም።

# የሳተናው ሊቀመንበር ሲሳይ አየለ ላይ ተከፈተው ዶሴ በዳኞች መካከል ግጭት  ፈጠረ

ሳተናው የድሬዳዋ ወጣቶች ንቅናቄ በሚል ሲቪክ አደረጃጀት ይታወቅ የነበረውና በቅርቡ የድሬዳዋ ነዋሪዎች አንድነት ፓርቲ በሚል ስያሜ የተደራጀው የፖለቲካ ተቋም ሊቀ መንበር አቶ ሲሳይ አየለ በድሬዳዋ ከተማ በእስር ላይ ይገኛሉ። የአቶ ሲሳይን የፍትሕ ሂደት ሲከታተል የቆየው ዳኛ ለችሎቱ ግልፅ ባልሆነ ሂደት ተቀይሮ ጉዳዩን ሌላ ዳኛ እንዲዳኘው ተደግጓል። ይህም ከመዝገብ ቤት መዝገቡን በመስረቅ የተዘዋወረ መሆኑን የባልደራስ ምንጮች ገልፀዋል። የሰነድ ስርቆትና የዳኛ ቅያሪ ያስፈለገው ዐቃቤ ሕግና ዳኛው በብሔር ተቧድነው ተከሳሹን ለመበቀል ነው በሚልም በዳኞች መካከል ግጭት ተፈጥሯል።

የመጀመሪያው ዳኛ ባይቀየር ኖሩ በሕጉ መሰረት የአቶ ሲሳይ የዋስትና መብት ሊጠበቅ እንደሚችልም ተጠቁሟል። በአሁኑ ጊዜ «አዲስ አበባ በጅ ፒ ኤስ ፈልጌ ነው ያገኘኋቸው። ይሰወሩብኛል።» በሚል የዐቃቤ ሕግ መከራከሪያ ምክንያት የዋስትና መብታቸውን እንደተከለከሉ ጠበቃቸው አቶ ዳዊት መስፍን ገልፀዋል።




አቶ ሲሳይ የተከሰሱት የባለሥልጣናትን ስም በማሕበራዊ መገናኛ ብዙሃን ማጥፋት በሚል ውንጀላ ነው። ይሁን እንጂ የፓርቲያቸውን እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ የተደረገ ፖለቲካዊ ክስ እንደሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ። ተከሳሹ የፊታችን ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም. በድሬዳዋ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ሲሆን ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ደግሞ በፌዴራሉ ፍርድ ቤት ካሉበት ሆነው በፕላዝማ ይቀርባሉ።

---

# ከዘጠኝ መቶ በላይ አማራዎች ከወለጋ ተፈናቀሉ

በኦሮሚያ ‹ክልል› ምዕራብ ወለጋ ሆሮጉድሩ ዞን ከዘጠኝ መቶ በላይ የአማራ ተወላጆች በአካባቢው የመንግሥት የሥራ ሓላፊዎች ትዕዛዝ ተፈናቅለው አማራ ምስራቅ ጎጃም፤ ግንደወይን ከተማ ገብተዋል። የተፈናቀሉት በአካባቢው በአነሳሽነትና በመንግሥት የሥራ ሓላፊዎች ትብብር እንደሆነም ተፈናቃዮች ገልፀዋል። የግንደወይንና አካባቢዋ ወጣቶች ለተፈናቃዮች የዕለት ደራሽ እርዳታ ለመስጠት እንቅስቃሴ እያደረጉ ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሰሜን ሸዋ ደራ አባት እና ልጅ በታጣቂዎች ተገድለዋል። በወቅቱ ሟቾች ሰብል በመሰብሰብ ላይ እንደነበሩ የገለፁት የመረጃ ምንጮች አስከሬናቸውን ለማንሳት የወረዳው የመንግሥት የሥራ ሓላፊዎችም ሆኑ ማሕበረሰቡ በፍርሀትና በቸልተኝነት ስሜት ዳተኝነት ማሳየታቸውን ገልፀዋል። በአካባቢው ካለፈው መስከረም ወዲህ ብቻ ከ15 በላይ ንፁሃን ተገድለዋል። ሰላም እንዲያስከብር የተጠየቀውና በአካባቢው የተሰማራው የኦሮሚያ የፀጥታ ኃይል «መሬቱን እንጂ ሕዝብ ልጠብቅ አልመጣሁም» ማለቱንም በደራ የሚኖሩ የመረጃ ምንጫችን ጠቁመዋል። ብሔርን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ሲፈፀሙ በዝምታ እንደሚመለከትም ገልፀዋል። የአነግ ታጣቂዎች ተደጋጋሚ ጥቃት ለማድረስ ቢመከሩም የሚያፈገፍጉት የአካባቢውን ገበሬ እንጂ መንግሥትን ፈርተው እንዳልሆነ ጨምረው ተናግረዋል። ደራ አማራዎች የሚኖሩበት የአማራ ግዛት መሬት ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ወደ ኦሮሚያ ‹ክልል› ተካሎ ይገኛል።

# የብሮድካስት ባለሥልጣን መረጃ ቴሌቪዥንን በሕገ ወጥነት ወነጀለ

በመገናኛ ብዙኃን ቁጥጥር እና ፈቃድ አሰጣጥ ሥራ ላይ የተሰማራው የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የመንግሥትን ገመናዎች በማጋለጥ፣ በመተቸትና ለህገራዊ ፖለቲካዊ ቀውሶች የመፍትሔ ሃሳቦችን በመጠቆም የሚታወቀውን መረጃ ቴሌቪዥንን በሕገ ወጥነት ወንጅሏል። ተቋሙ በዋና ሥራ አስኪያጁ በተፃፈ ደብዳቤ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሳተላይት ቴሌቪዥን ጣቢያው ላይ ርምጃ እንዲወስድ ጠይቋል።

መረጃ ቴሌቪዥን በራሱ ባለሙያዎች ከሚሠራቸው ፖለቲካዊ ዘገባዎችና ፕሮግራሞች በተጨማሪ በፖለቲካ ትንታኔ ሰፊ ልምድ ካላቸው ተባባሪ አዘጋጆች ጋር በጥምረት በመሥራት በበርካታ ኢትዮጵያውያን ተመልካቾች ዘንድ ሰፊ ተቀባይነትን ያገኘ ጣቢያ ነው። ከተባባሪ አዘጋጆቹ መካከል ታዋቂዎቹ የፖለቲካ ተንታኞች ኤርሚያስ ለገሰ፣ ሐብታሙ አያሌው፣ ርዕዮት ዓለሙ፣ ቴዎድሮስ ፀጋዬ እና ሌሎችም ይገኙበታል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በመምህርነቱ የሚታወቀውና የአብይ አሕመድ አገዛዝ ቤተክርስቲያን ላይ እያደረሰ ያለውን ጥቃት ፊት ለፊት የሚያጋልጠው ዘመድኩን በቀለም ከሰሞኑ በተባባሪ አዘጋጅነት ቴሌቪዥን ጣቢያውን ተቀላቅሏል።

መረጃ ቴሌቪዥን የሳተላይት ስርጭቱን ከመጀመሩ አስቀድሞ ለረዥም ጊዜ በሳይበር መገናኛ ብዙኃንነት ሲያገለግል ቆይቷል።

# የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት እንዴት?

***ታሪካዊ መነሻ***

ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔረተኞች ሊያሳምኑን እንደሚፈልጉት የአዲስ አበባ ከተማ የተመሠረተችው በአጼ ምንሊክ መሪነት የኢትዮጵያ መንግሥት ከኦሮሞ ጎሳዎች በኃይል በቀሙት መሬት ላይ አይደለም:: አጼ ምንሊክና እቴጌ ጣይቱ ዳግማዊት በራራ የሆነችውን አዲስ አበባን ከመቆርቆራቸው በፊት በአንኮበር፣ በመናገሻ፣ ከዚያም ወጨጫና ወደ መጨረሻም እንጦጦ ላይ ሰፍረው ነበር:: እነዚህን ቦታዎች በጊዜያዊነት ለመስፈሪያነት የተቀመጡባቸው ቢሆንም ለዋና ከተማነት ያልመረጧቸው አካባቢዎቹ ዋና ከተማ ለመመሥረት አመቺ ስላልነበሩ አይደለም:: አያት ቅድመ አያቶቻቸው አንድ ምዕተ ዓመት ከግማሽ ለሚያህል ጊዜ /ከ1382-1531/ የከተሙባትን፣ የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የነበረችውን በራራን ፈልጎ ለማግኘትና የበራራ ፍርሥራሽ በተገኘበት ቦታ ላይ አዲስ አበባ ብለው እቴጌ ጣይቱ የሰየሚትን ዳግማዊት በራራን መልሶ ለመገንባት በማለም ነበር :: ስለዚህ ነው በራራ ቀዳሚት አዲስ አበባ የተባለችው:: የበራራ ከተማ ፍርሥራሽዋ የተገኘው ደግሞ ከወጨጫ፣ ከእንጦጦና ከየረር የተራራ ሰንሰለቶች መሃል እንደሆነ የውጭ አገርና የሀገር ውስጥ የታሪክ ጸሐፊዎች የተገኘውን ፍርሥራሽ በፎቶግራፍ አስደግፈው በመጽሐፍት የሰነዱት ሐቅ ነው::

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴ፣ የአጼ ምኒሊክ አያት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ አዲስ አበባ ላይ የልጅ ልጃቸው ከተማ ቆርቁሮ አገር እንደሚያስተዳድር ትንቢት መናገራቸውን እንደሚከተለው ገልጸዋል:: «ከትልቁ ዛፍ ከማዎቱ አጠገብ ተቀምጠው ጠጅ በቀንድ ቀርቦ ሠንጠረዥ እየተጫወቱ አንቺ አገር ዳዋ ሠፍሮብሻል:: ኋላም የልጅ ልጄ ቤት ይሠራብሻል፤ ከተማ ያደርግሻል» ማለታቸውን በመጽሐፋቸው አስፍረዋል:: (ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ 1959 ዓ.ም.)

በራራ ወይም ቀዳሚት አዲስ አበባ በግራኝ አህመድ ጦር በ1531 ዓ.ም ተቃጥላ ከወደመች በኋላ አሸናፊው የግራኝ ጦር ከሸዋ ወደ ሰሜን መነቃነቁን፣ የአጼአዊ ማዕከላዊ መንግሥቱ እና የግራኝ ጦር ሰራዊት የፍልሚያና የዘመቻ ስምሪት ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እየራቀ መሄዱን የተረዱት የበረይቱማ እና የቦረን የኦሮሞ ጎሳዎች እነሱ ከመድረሳቸው በፊት በቦታው የነበሩ የአማራ፣ የጉራጌ፣ የጋፋት፣ የአርጎባ፣ የማያ እና ሌሎች ማህበረሰቦችን በኃይል አስወግደውና አፈናቅለው በቦታው ላይ በቋሚነት ሊሰፍሩ ቻሉ:: በዚህ አጋጣሚም አብዛኛው ሸዋ ከማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ስር ለመውጣት በቃ::

ቀዳሚት አዲስ አበባ የነበረችው የበራራ ከተማ ከመቃጠሏ በፊት በራራ መካነ መንግሥት እና መካነ ጳጳስ እንዲሁም መስጊዶች የነበሩባት፣ የጀርመን፣ የስፔን፣ የፈረንሳይ፣ የፖርቹጋል፣ የኢጣልያን ልዩ ልዩ ግዛቶች አምባሳደሮች የተስተናገዱባት፣ ኢትዮጵያ ከአውሮፓና እስያ ጋር በዓለም አቀፍ የንግድ መስመር የተሳሰረችበት ከተማ ነበረች:: በራራ የቬኒስ፣ የሊዝበን፣ የሲሲሊ፣ የማርሴይ፣ የኔፓልስ የጥበብ ሰዎች የሚያዘወትሯት፣ ከአራት የተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚነሱ አውራ ጎዳናዎች እና የንግድ መስመሮች የሚገናኙባት መላ ኢትዮጵያ በንግድ የተሳሰረባት ከተማ ነበረች:: በራራ ከተማ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በመሆን ያገለገለችው ከሮሃ-ላሊበላ በኋላ እና ጎንደር የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ከተማ ሆኖ ከመቆርቆሩ በፊት ባለው የመካከለኛ ዘመን የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ነው::

በዘመናዊ ኢትዮጵያ ታሪክ አጼ ምንሊክ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት አስተዳደር ስር ያስገቧቸው ነገዶች የጥንት እና የመካከለኛ ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት ያስተዳደሯቸው የሀገረ ኢትዮጵያ አካል የነበሩ ናቸው:: ከአክሱም ዘመን ጀምሮ እስከ 1966ዓ.ም በተከታታይነትና በልሙጥነት የዘለቀው የኢትዮጵያ ዘውዳዊ መንግሥት በስሩ ሲያስተዳድራቸው በቆዩ ነገዶች መካከል የሙብት ልዩነት ሳይደረግ፣ በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ነገዶች መካከል የነበረውን የሃይማኖት፣ የቋንቋና የባህል ልዩነት የተቀበለ የህግና የአስተዳደራዊ ስርዓት ዘርግቶ አገሪቱን ሲያስተዳድር እስከ አጼ ምንሊክ ዘመን ድረስ የዘለቀ ነው::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዙፋኑን ከንግሥት ዘውዲቱ ከተረከቡ በኋላ እስከ 1928 ዓ.ም የጣሊያን ወረራ ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ መሻሻሎች ብታደርግም ከአጼ ምንሊክ ዘመን ከነበረችበት ሁኔታ ብዙም ለውጥ አልታየባትም ነበር:: ከ1923 ዓ.ም እስከ 1928 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ አስተዳደር በ44 አውራጃዎች ተከፋፍሎ ይስተዳደር የነበረበት ጊዜ ሲሆን፣ አዲስ አበባ ከ44ቱ አውራጃዎች መካከል 44ኛና የአገሪቱ ዋና ከተማ ሆና በራስ ገዝ አውራጃነት ተዋቅራ ነበር:: ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወራ የኢጣልያ ጦር አዲስ አበባ ከገባ ከ1928 ጀምሮ በሽንፈት ኢትዮጵያን እስከለቀቀበት እስከ1933 ዓ.ም ድረስ በነበሩት አምስት ዓመታት አዲስ አበባ በመሠረተ ልማትና በህንፃ ግንባታዎች ረገድ ከፍተኛ እምርታ ያስመዘገበችበት ጊዜ ነበር:: ኢጣልያ ኢትዮጵያን ይዛ በቆየችባቸው አምስት ዓመታት የኢጣልያ የቅኝ ግዛት አስተዳደር ኢትዮጵያን በስድስት ግዛቶች በመከፋፈል ያስተዳድር ነበር:: እነሱም:-

1. የኤርትራ አስተዳደር /ትግራይን እና ኤርትራን ያጠቃለለ ዋና ከተማ አስመራ/
2. አማራ አስተዳደር /በጌምድርንና ሰሜንን ፣ ወሎን፣ ጎጃምን ያጠቃለለ - ዋና ከተማ ጎደንር/
3. አዲስ አበባ - የመላ የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ዋና ከተማ /ኤርትራ፣ ደቡብ መካከለኛ ሱማሌ፣ ኢትዮጵያን አካቶ/
4. ሸዋ - ዋና ከተማ አዲስ አበባ
5. ጋላና ሲዳማ ብሎ ኢጣልያ የጠራው - ዋና ከተማ ጅማ
6. ሐረርጌንና ባሌን ጨምሮ - ዋና ከተማ ሐረር

የኢጣልያን ወረራ አብቅቶ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ወደ ዙፋኑ በ1933 ዓ.ም. ሲመለስና በዚሁ ዓመት ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የአገረ-ግዛት ሚንስቴር ሲቋቋም ኢትዮጵያ በ12 ጠቅላይ ግዛቶች እንድትዋቀር ተደረገ። በ1940 ዓ.ም ባሌን ከሐረርጌ በመለየት ባሌ 13ኛ ጠቅላይ ግዛት ስትደረግ አዲስ አበባ ልዩ ጠቅላይ ግዛት ተብላ በ14ኛ ጠቅላይ ግዛትነት የኢትዮጵያ ዋና ከተማና የ13ቱም ጠቅላይ ግዛቶች ማዕከል ሆና ተዋቀረች።

በንጉሱ ዘመን አዲስ አበባ ውስጥ እያንዳንዱ 14 ጠቅላይ ግዛቶች ጽ/ቤት ነበራቸው። የእያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ወደ ማዕከላዊ መንግሥት ግብር የሚያስገባው አዲስ አበባ ውስጥ ባለው ጽ/ቤት አማካይነት ነበር። እያንደንዱ ጠቅላይ ግዛት በአዲስ አበባ ውስጥ ባለው ላይዘን ጽ/ቤት አስተባባሪነት ሽቀጣ ሸቀጥ ወደየጠቅላይ ግዛቱ የሚወስድበት ልዩ ግዛት ነበረው። አዲስ አበባ የሁሉም ጠቅላይ ግዛቶች ማዕከል ስለነበረች ከተማዋ የተገነባችው በሁሉም ኢትጵያውያን ግብር ላብና ድካም ነው። ማናቸውም ኢትዮጵያዊ አዲስ አበባ የጋራ ከተማችን ናት የሚለውን ፖለቲካ ሊደግፈው የሚገባው የአሁኑ ዘመን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አያቶችና ቅድመ አያቶች የገነቡዋት ከተማ በመሆኗ ነው። በ1952 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትዋሃድ አዲስ አበባን ጨምሮ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች 14 ሲሆኑ፣ አዲስ አበባ በልዩ ጠቅላይ ግዛትነት ደረጃ የራስ ገዝነት እርከን እንደያዘች ቀጠለች። ይህ የአገሪቱ መንግሥት አወቃቀር እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ ቀጠለ። በንጉሡ ዘመን አዲስ አበባ በአዋጅ ልዩ ጠቅላይ ግዛት ሆና ራሷን ችላ በምትደዳደርበት ጊዜ አራት አውራጃዎች፣ 10 ወረዳዎች በርከት ያሉ ምክትል ወረዳዎች ይዛ ስፋቷ 122,000 ሄክታር ነበር። በደርግ ዘመን አዲስ አበባ ይህንኑ ስፋቷን እንደያዘች ቀጥላለች።

## ያለፉት 50 ዓመታት የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት አስተዳደር ልምድ

በደርግ ዘመን መጀመሪያ ማለትም በ1968 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማን የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ ለመደንገግ የደርግ መንግሥት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 80/1968 ጋር አባሪ ተደርጎ የቀረበው የከተማዋ ካርታ ከተማዋ የትኞችን በዙሪያዋ የሚገኙ ቦታዎች እንደምታካትትና ስፋቷም 122,000 ሄክታር እንደነበር ተመልክቷል። በካርታው ውስጥ አሁን "የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን" በሚል የተካተቱ ቦታዎች በአዲስ አበባ የቀድሞ ይዞታ ስር እንደነበሩ በግልጽ ተመልክቷል። /ካርታው ከነአዋጁ በአባሪነት ቀርቧል/

በደርግ ዘመን በ1981 የራስ ገዝ አካባቢዎችን፣ የአስተዳደር አካባቢዎችንና የአውራጃዎችን ለመወሰን አዋጅ ቁጥር 26/1981 በታወጀበት ጊዜ አዋጁ አዲስ አበባን በ13 የከተማ ክ/ከተሞች፣ በ20 የገጠር አውራጃዎች ከፍሏቸው ነበር። ክ/ከተማዎቹ አራዳ፣ ተከለሃይማኖት፣ አዲስ ከተማ፣ ኮልፌ፣ ጉለሌ፣ ቀጨኔ፣ እንጦጦ፣ የካ፣ ቦሌ፣ ንፋስ ስልክ፣ ቂርቆስ፣ ልደታ፣ ኮተቤ ሲሆኑ የገጠር የአዲስ አበባ አውራጃዎች ደግሞ በሰቃ፣ በረህ፣ ዓለምገና፣ ወልመራ፣ ሱልልታና አቃቂ ነበሩ። እነዚህ የአዲስ አበባ የገጠር አውራጃዎች በሥራቸው 25 ወረዳዎች ነበሯቸው። /ዝርዝሩ ከዚህ መግለጫ ጋር በአባሪነት ተያይዟል/።

ከላይ እንደተጠቀሰው ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ ጊዜ ድረስ የአዲስ አበባ ስፋት 122,000 ሄክታር እንደነበር ልብ ይሏል። አዲስ አበባ በውሃና እህል አቅርቦት ረገድ ራሷን የቻለች ከተማ ነበረች። የገፈርሳ ወንዝ በአቃቂ ዙሪያ የሚገኘው ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ በአዲስ አበባ ከተማ ይዞታ ስር ነበር። በአዲስ አበባ ይዞታ ስር በከተማዋ ዙሪያ የነበሩ በርካታ የቀበሌ የገበሬ ማህበራት ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ማለትም የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የጉራጌ እና ሌሎች የደቡብ ብሔረሰቦች፣ ከኤርትራ ሃማሴን ሳይቀር ባጠቃላይ ከመላው ኢትዮጵያ የመጡ ሰዎች መሬት ከባለ መሬት እየተከራዩ የተለያዩ የጓሮ አትክልት እና የእህል ሰብል የሚያመርቱ ገበሬዎች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ነበሩ። በአጭሩ አዲስ አበባ ሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ዜጎች መጥተው ኑሯቸውን የሚመሠርቱበት፣ በገበሩት ግብር ያለሟት፣ የክፍለ ሀገር ኑሮ እድገታቸውን/ መሻሻላቸውን እንደሚገታ ሲገምቱ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የሚመጡባትና የሚጠለሉባት ከተማ ሆና የኖረች ናት።

አዲስ አበባ አሁን የሚኖርባት ነዋሪ አባቶችና ቅድመ አያቶች ከየቦታው እየመጣ መኖሪያ እና መጠለያ ያደረጋት ናት። እስከ ህወሓት ዘመን ድረስ ኦሮሚያ የሚባል ግዛት / ክልል/ አልነበረም። ባለፉት 30 ዓመታት ወያኔ ከአማራው ክልል መሬት ነጥቆ ወደ ትግራይ እንደከለለው ሁሉ ህወሓት እና ኦነግ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ታሪክ የማይታወቅ ኦሮሚያ የተሰኘ ክልል ፈጠረ። ይሄ አይነት አከላለል በኢትዮጵያ የጥንትም ሆነ የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚታወቅ አይደለም። ይሄ አዲስ ክልል ነው። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የሽግግር ወቅት በመባል የሚታወቀው ከሰኔ 1983 - ነሐሴ 1987 በነበሩት አራት ዓመታት ውስጥ አዲስ አበባ ክልል 14 ተብላ እንደ ሌሎች የህወሐት/ኢህአዴግ ክልሎች ራሷን የቻለች ክልል እንደነበረች የሚታወቅ ነው። ህወሓት ኢህአዴግ በተለይ ከ1997 በምርጫ ሽንፈት ከገጠመው በኋላ (መንግሥት ውጤቱን በጉልበት ቢቀይረውም) የአዲስ አበባ ይዞታ በየጊዜው እየጠበበ እንዲሄድ እና ጽንፈኛ ብሔርተኞች የራሳችን ነው ወደሚሉት ኦሮሚያ እንዲካለል እና የአዲስ አበባ ይዞታ ቀደም ሲል ከነበረው እንዲቀንስ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከከተማው ነዋሪ እጅ ወጥቶ በሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲገባ አደረገ።

በህወሓት/ኢህአዴግ ኦነግ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49፣ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አዲስ አበባ የፌዴራል መንግሥቱ ዋና ከተማ መሆኗ ተመልክቷል። አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ሰጥቶታል። ከ1987 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ በየጊዜው ሲሻሻሉ የቆዩ ቻርተሮችም ቢሆኑ የከተማዋ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ መብት እንዳለው አስረግጦ አስፍሯል። የኢፌድሪ ህገ መንግሥት የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ ማስተደዳር ይችላል የሚል ድንጋጌ ቢኖረውም ለይስሙላ ተባለ እንጂ የአዲስ አበባ ሕዝብ የሀገሪቱ የፌዴራል ሥርአት እንደሚደነግገው፣ ነዋሪው ራሱ በመረጣቸው ሰዎች ተዳድሮ አያውቅም። ባለፉት 30 ዓመታት ሌሎች ክልሎች ለይስሙላም ቢሆን ከየክልላቸው በተመረጡ ሰዎች ሲመሩ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ይህ መብት እስካሁን ድረስ ተነፍጓቸው ከሌሎች ክልሎች በሚመጡ ሰዎች የሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲወድቁ ተደርገዋል።

ከላይ በቀረቡ ተጨባጭ መረጃዎች እንደተመለከተው አዲስ አበባ በዙሪያዋ ይኖሩ የነበሩ ገበሬዎች በከተማ ቀመስ የገበሬ ማህበራት ስር የታቀፉ ነበሩ። ወደ በኋላ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ምክንያት ተፈናቀሉ የተባሉት ገበሬዎች ይኖሩበት የነበረው የአዲስ አበባ ዙሪያ አካባቢ ከአዲስ አበባ ተቆርጦ "የፊንፊኔ ልዩ ዞን" በሚል ከአዲስ አበባ በተወሰደ መሬት

ላይ የሚኖሩ ገበሬዎች ነበሩ። እውነተኛው ክንውን የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን የተቀየሰው ከአዲስ አበባ በተቀማው የከተማዋ መሬት ላይ እንጂ ከኦሮሚያ ክልል በተወሰደ መሬት ላይ አይደለም።

Get'ye Yalew, [26.10.20 16:07]

ከ1997 ዓ.ም የህወሓት ሽንፈት በኋላ አቶ መለስ ዜናዊ ኦህዴድን ከናዝሬት/አዳማ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ አደረጉ። የአዲስ አበባ ይዞታ ቀድሞ ከነበረበት የቆዳ ስፋት ወደ 54.000 ሄክታር እንዲጠብ ተደረገ። ከ1997 ዓ.ም በኋላ ህወሓት በአዲስ አበባ ዙሪያ ብዙ የጋራ መኖሪያ ቤቶች መሥራት ሲጀምር ከተማዋ እየተለጠጠች ከኦሮሚያ ክልል ጋር "የድንበር አለመግባባት" ችግር ተፈጠረ። የድንበር አለመግባባቱ የተፈጠረው የአዲስ አበባ የቀድሞ ይዞታ የነበረውን ህወሓት ከአዲስ አበባ ነጥቆ " የፊንፊኔ ልዩ ዞን" በሚል ወደ ኦሮሚያ እንዲካለል በማድረጉ ነው። የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት በ2009 ዓ.ም በዶ/ር ዐብይ የሚመራ ኮሚቴ የአዲስ አበባን ከተማ ከኦሮሚያ እና ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የተውጣጡ ባለሙያዎች እንዲያጠኑት ተደረገ። በተደረገው ጥናት በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያለው ይዞታ ከ54,000ም ሄክታር እንደሆነ ቢገለጽም በተጨባጭ ግን የጥናቱ ውጤት ያሳየው በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር ሆኖ የተገኘው ወደ 51,355 ሄክታር ቀንሶ ተገኘ። ይህም የሆነው ምንም አይነት አዋጅ ሳይደነገግ በውስጥ ለውስጥ አሠራር ነው። በአዲስ አበባ ዙሪያና በአዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩት እን ሰበታ፣ ሰንዳፋ፣ ኮተቤ አንቁርጫ፣ የካ አባዶ፣ የካ ጣፎ፣ ቦሌ ኮተቤ፣ ሱልልታ፣ (በበሰቃ ውስጥ አቃቂና አቃቂ ከተማ፣ ሰርቲ፣ ከዩ፣ ገላን ጎራ፣ ቂሊንጦ፣ ፊጨ፣ ቀርሳ፣ ቱሉ ሜጫ) በረህ፣ ዓለም ገና፣ ወልመራ፣ ወዘተ...ወደ ኦሮሚያ ክልል እንዲጠቃለሉ መደረጉ ይታወሳል። ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን ጥናት በተመለከተ የተቀሰቀሰውን ተቃውሞ ምክንያት በማድረግ በኦህዴድ ውስጥ ውዝግብ ተነሳ። ይኸውም፡- በእነአቶ ድሪባ ኩማና በአቶ ኩማ ደመቅሳ በኩል አዲስ አበባ ከ1997 ምርጫ በኋላ ሕወሓትና ኦህዴድ ተስማምተው በወሰኑላት የ54,000 ሄክታር ይዞታ መጠን ላይ መሆን አለባት ሲሉ፣ በዶ/ር ዐብይና በአቶ ለማ በኩል ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ይዞታ ወደ 43,000 ሄክታር ዝቅ ማለት አለበት የሚል አቋም ያዙ። ይህ ውዝግብ መቋጫ ሳያገኝ በመጋቢት 2010 ዓ.ም ህወሓት/ኢህአዴግ ቦታውን ለኦህዴድ ለቀቀ። ኦህዴድ ውስጥ አሸናፊ ሁኖ የወጣው የጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ አመራር ቀደም ሲል ባቀረበው ሃሳብ መሠረት ከአዲስ አበባ 30 ወረዳዎች ተቀንሰው ወደ ኦሮሚያ ይካለላሉ ማለት ነው። ይህም ወደ ዝርዝር ሲተረጎም ከየካ ክ/ከተማ 6 ወረዳዎች፣ ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ 1 ወረዳ፣ ከአቃቂ ክ/ከተማ 7 ወረዳዎች፣ ከጉለሌ ክ/ከተማ 5 ወረዳዎች ፣ ከቦሌ ክ/ከተማ 2 ወረዳዎች እና ከኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ 9 ወረዳዎች በኦሮሚያ ይጠቀለላሉ። አሁን በወ/ሮ አዳነች አበቤ ምክትል ከንቲባነት ዘመን ቀደም ሲል በዶ/ር ዐብይ አህመድ ሲመራ የነበረው ኮሚቴ ሲያራምድ የነበረውን 30 ወረዳዎች፣ ከአዲስ አበባ ቀንሶ ወደ ኦሮሚያ የማካለል ፍላጎት አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል ሙሉ ጥገኝነት ስር እንድትወድቅ ለማድረግ ያለመ ነው። ይህ አካሄድ አዲስ አበባን በኢኮኖሚ ረገድ እንደቀድሞዋ ራሷን እንዳትችል እና ከኦሮሚያ ክልል በምታገኘው ልዩ ጥቅም ተንበርካኪ እንድትሆን የሚያደርግ አካሄድ ነው።

በኦሮሞ ብልጽግና ብቻ ሳይሆን በሁሉም የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የተደረሰው ስምምነት አዲስ አበባ በህገ መንግሥቱ የተሰጣትን የራስ በራስ አስተዳደር በመንጠቅ ልዩ ጥቅም የሚለውን ግልጽ ያልነበረ እስካሁንም ዝርዝር ሕግ ያልወጣለት የሕገ-መንግሥት አንቀጽ ሰርዞ፣ ሙሉ ለሙሉ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በባለቤትነት እንድትካተት ማድረግ ነው። በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ረገድ በዶ/ር ዐብይ መንግሥት እየተከናወነ ያለው ተግባር በጥሞና ሲታይ ወደዚህ ግብ የሚያመራ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። ኦህዴድ/ብልጽግና እና በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በመደገፍ የኦሮሞ ጽንፈኛ ብሔርተኞች በአዲስ አበባ ላይ ያነሱት የባለቤትነት ጥያቄ «ከታሪክ የሚቀዳ ነው» የሚል ከታሪክም፣ ከህግም፣ ከአስተዳደራዊ አወቃቀር ልምድም አንፃር ያፈነገጠ አሠራር ነው። ይህ ድርጊት ደግሞ ታሪክን በተንሸዋረረ መነጽር ከመመልከት የመነጨ አባዜ እንጂ የነሱ የባለቤትነት ጥያቄ ከተጨባጭ የታሪክ ማስረጃዎች አንፃር ውሃ የሚቋጥር ሆኖ አይደለም።

በተጨባጭ ማስረጃ የሚደገፈው ታሪክ መሃል ኢትዮጵያ በኦሮሞ ጎሳዎች ከመወረሩ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት አዲስ አበባና አካባቢዋ ብቻ ሳትሆን መላ ሸዋ የአማራ፣ የጉራጌ፣ በሂደት ወደ አማራነት የተለወጡ የሃርላ እና የጋፋት ሕዝቦች አጽመ ርስት የነበረ መሆኑ ነው። ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔርተኞች ይዞታ ከታሪክ ይቀዳል በሚል አካሄዳቸው "ከአጼ ምንሊክ ጀምሮ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ ኦሮሞ በነፍጠኛው ሥርዓት በቅኝ የተገዛበት ታሪክ ነው፤ ነፍጠኛን በሰበረን ቦታ ሰብረነዋል፤ አሁን ኦሮሞ ሥልጣን ከያዘ አዲስ አበባን በባለቤትነት እንጠቀልላለን" በሚል የተሳሳተ የታሪክ ትርክታቸው ከፀኑ እነሱ ሙልጭ/በዜሮ/ የሚወጡበትን አካሄድ እየተከተሉ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል። የኦሮሙማ አቀንቃኝ ጽንፈኛ ብሔረተኞች «ሁሉም የኛ ነው» ከሚል ለከት የለሽ አካሄዳቸው ታቅበው፣ ኢትዮጵያም ሆነች አዲስ አበባ የሁላችንም ኢትዮጵያውያን የጋራ ይዞታዎች መሆናቸውን መቀበል ይኖርባቸዋል። ከዚህ ውጭ ያለው አካሄድ የርስ በርስ ጦርነት ከመጋበዝ እና በሁሉም ላይ ጥፋት ከማስከተል ውጭ ማንም ወገን ለብቻው የሚያተርፍበት ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል በውል ሊያስተውሉት ይገባል።

እንደ ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ እምነት የአዲስ አበባ ጉዳይ ወደ ቀድሞው ይዞታዋ መመለስ ይኖርባታል። ይህ ማለትም የይዞታ ዳር ድንበርን በተመለከተ አዲስ አበባ በአጼ ኃይለሥላሴ፣ በወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እና በኢሕአዴግም እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ ወደ ነበረው የ122,000 ሄክታር ይዞታዋ መመለስ ይገባታል። የራስ ገዝ አስተዳደር ጉዳይንም በተመለከተ በአጼ ኃይለሥላሴ፣ በደርግ እና በህወሓት/ኢህአዴግ የሽግግር ወቅት ዘመናት ወደነበረችበት የራስ ገዝ አድያም/ክልል የአስተዳደር ደረጃ መመለስ ያስፈልጋል። በ1987 ዓ.ም. የፀደቀውና እስካሁን ያልተሻረው የኢፌድሪ ህገ መንግሥት በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አዲስ አበባ ከሞግዚት አስተዳደር ስር ወጥታ ነዋሪው በነፃነት በመረጣቸው ወኪሎቹ ሊተዳደር ይገባል። የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት ጥያቄ በታሪክም ሆነ በሕግ የተደገፈ መሆኑን እድሜው ከ30 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው እና የሚያስታውሰው ስለሆነ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እና የፖለቲካ ኃይሎች ሊደግፉት ይገባል እንላለን። ስለዚህ በዜግነት ዙሪያም ሆነ በክልል ደረጃ የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ከሰማንያ በላይ ከሆኑ ብሔረሰቦች በተውጣጡ ዜጎች ላብ የተገነባች መሆኗን በመረዳት እና እውነተኛ ታሪካዊ ዳራውን በማጤን እራሷን እንድታስተዳድር ሙሉ ተግባራዊ ድጋፋቸውን እንዲያበረክቱ ታሪካዊ፣ ሕጋዊ እንዲሁም ሞራላዊ ኃላፊነት ወድቆባቸዋል።

ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ያነሳውን የአዲስ አበባ ከተማ የተሟላ የራስ ገዝነት ጥያቄ፣ አዲስ አበባ የመላ ኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መገናኛ እና ማዕከል ሆና ማገልገል አለባት የሚል አቋም ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች/ድርጅቶች ደግፈው በጋራ እንዲቆሙ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል።

(ክፍል 2 ይቀጥላል)

# አብን የጠራው ሰልፍና የተቋማትና የግለሰቦች ማስጠንቀቂያ



ወግደረስ ጤናው

ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ኢትዮጵያ ከነበራት ጠንካራ ሎዓላዊ ክብር ወርዳ ኮስሳ የታየችበት ጊዜ ነበር:: ኢትዮጵያን በጠላ መዳፋ በትውድቅ እንኳን ያ የነበራት ሉዓላዊ ግርማ ሞገስ አሁን ባለው ደረጃ ኮስምኖ ይታያ የሚል እምነት እንደማይኖራቸው በሀገር ግንባታ ሂደት ግምበር ቀደምት የሆነች አባቶች ያነሳሉ:: ዛሬ ግን ኢትዮጵያ ተዋርዳለች:: አምጣ በወለደቻቸው ልጆቿ ተንኮል ሞገሷ ጠፍቷል:: ክብሯ ጎድፏል:: የዘውጌ ፖለቲከኞች ለሥልጣናቸው ማደሪያ ሲሉ አጥንት ጉልጥምት እየቆጠሩ ትልቋን ሀገር 10 ትናንሽ አድርገዋታል:: ዜጎች እንኳንስ በባዕዳን ቀዬ እትብታቸውን በቀበሩበት መታፈራቸው ቀርቷል:: ኢትዮጵያን ጥሎ መስደድ ቅንጦት ሆኗል:: መፈናቀል ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በምድርና በሰማይ እሳት የሚወርድባትን ሶሪያን አስንቀን ምልክታችን አድርገነዋል:: እድሜ ልክ በደምና ወዝ፣ በተገነቡ ንብረቶች በብርሀን ቅፅበት ወደ አመድነት በየጊዜው ሲለወጥ ማየት ብርቅ አይደለም:: መግደልንና መሞትን በየአይነቱ አይተነዋል:: ንፁሃንን በመንጋ በድንጋይ ቀጥቅጦ ገድሎ ዘቅዝቆ ከመስቀል ጀምሮ፤ የሰው እስከሬን ገፎ ኩላሊት አውጥቶ በጥሬው የሚበላበትን ሁኔታ ሳይገርመን ቁጭ ብለን አይተናል:: ሰምተናል:: ኢትዮጵያዊያን ዛሬ ላይ የምንኖርባት እውነት ይህ ነው:: ይህንን ኢ- ሰብዓዊ የሆነ አረመኔያዊ ድርጊት ለማውገዝ ዜጎች ድምፃቸውን ሲያሰሙ "አድርባይነት ከጦርነት በላይ የከበዳቸው" የመንግሥት ካድሬዎች በማህበራዊ ትስስር ገፆችና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ተጠቅመው ጉዳዩን ሲያጣጥሉ ይስተዋላሉ:: አልፎም በአንድ ብሔር ማዕቀፍ አውጋዞን ግለሰብ ይፈርጃሉ:: በዚህ አምድ ላይ በተለይም የጥቃቱ ሰለባ በሆነውን የአማራ ሕዝብ ቁስል ላይ ጨው ለመነስነስ ሳይሆን ላለፉት ሰላሳ ዓመታት በብሔር ፌደራሊዝሙ ሰበብ የአማራን ሕዝብ ስነ ልቦና ሳይረዱ እንወክለዋለን በሚል እስካሁኗ ሰዓት ሲያስገድሉ፣ ሲገድሉና ሲያፈናቅሉ ለባጁት ለጌቶቻቸው በፍፁም ታማኝ ባርነታቸው ለሚታወቀው በአዴን/ አዴፓ ከሰሞኑ አብን (አማራ ብሄራዊ ንቅናቄ) በአማራ ክልል ከተሞችና በአዲስ አበባ የጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ እውቅና አልሰጥም ማለቱን ተከትሎ በሀገር ውስጥም በውጭም የደረሰበትን ከፍተኛ ውግዘት ለማንሳት ነው::

## ብአዴን/ አዴፓ ሰልፉን አስመልክቶ ምን ምላሽ ሰጠ?

ጥቅምት 16/2013 ዓ.ም ባሕር ዳር አቶ ግዛቸው ሙሉነህ፤ የአማራ ‹ክልል› መንግሥት ቃል አቀባይ "አሁን የገጠመን ችግር በሰልፍ የሚፈታ ቢሆን ኑሮ የክልሉ መንግሥት ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዶ በበላይነት ባስተባበረው ነበር" ብለው ይጀምራሉ:: በመግለጫው የክልሉ ኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር ይለጥቁና ...... "የአማራ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደር፣ የራሱ ባህል እና አኩሪ ታሪክ ያለው ሕዝብ ነው፤ የአማራ ሕዝብ አሁን ለመጣው ለውጥ ብዙ ዋጋ እና መስዋዕትነት የከፈለ ሲሆን በመስዋትነቱም ይህን ለውጥ አምጥቷል::

ስለሆነም የአማራ ሕዝብ የለውጡ አካል ነው፤" ሲሉ ይገልፃሉ:: ከዚህ ንግግራቸው እንደምንረዳው ትህነት/ ኢህአዴግ ዛሬ ላይ ከማዕከላዊ ሥልጣኑ ተገፍቶ በመንደርደር መሪነት እንዲወድቅ ትልቁን የህይወት፣ የአካልና የገንዘብ አስታዋፆ በቀዳሚነት እንደከፈለ ይመሰክራል:: በመጣው ለውጥ ግን የተረፈውን ዘለው፣ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ "ለውጡን በተመለከተ ሁለት ኃይል ተፈጥሯል ይላሉ"::.....

"አንደኛው ኃይል ብዙ ዋጋ ተከፍሎ የመጣው ለውጥ ( የኳልዮሽ ለውጡ ከይሆን አይቀርም) እንዳይቀለበስ ትግል የሚያደርግ ሲሆን የታፈነው አህዴድ ብልፅግናን ማለታቸው ይመስላል)፤ ሁለተኛው ኃይል ደግሞ በለውጡ ውይድር የተገፋው በተደራጀና መዋቅራዊ በሆነ መንገድ ሀገርን ሲበዘብዝ የነበረው፤ ፀረ ዴሞክራሲያዊ እና ከአምባገነኑ ኃይል ሲሆን የሥልጣን መንበሩን ለመመለስ እንዲሁም ለውጡን ለመቀልበስ እየሠራ ያለው የጥፋት ኃይል ወይም ቡድን ነው::" ሲሉ ይገልፃሉ:: እኛ ላይ በነገሩን መግለጫቸው፣ የመኖር ተፈጥሮአዊ መብቱን የጠየቀውን የአማራ ሕዝብ በለውጥ እስከጠየቅናቸው በለውጥ ነጣቂዎች ግብግብና በታሪክ የዚህ አነንዳ አራማጆች ዛሬ ላይ ያለገላጋይ በየቦታው አሳሩን እየበላ እንደሆነ ይታያል:: ዋና ዳይሬክተሩ ከፍፍ ይሉና "አማራ የሀገረ መንግስቱ የድርብ አጥንት እና በኢትዮጵያዊነቱ እንደማይደራደር የተረዱ ኃይሎች በአማራ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች ጥይትና ግድያ በመፈፀም ህዝባችን ከኢትዮጵያዊነት እንዲወርድ በርካታ

ግፎች እየተፈፀመበት ይገኛል:: የዳይሬክተሩ በዚህ ንግብራቸው ያስነቃቸው የሚመስለው የአማራው ከኢትዮጵያዊነት መውረዱ እንጅ፤ በየጉደበው በካራ አንገቱ እየተቀነጠሰ ያለቀባሪ መቀረቱ አይደለም:: በ27 ዓመቱ በትህነግ/ኢህአዴግ ጉዞ ላይ አማራውን በመንደር አውርደው ሲከልሉት ያለ ልኬት የተሰመረበት አርቴፊሻል መስመር እንዳልሆነ ገልፃ ኢትዮጵያዊ ነኝ በማለቱ አማራ ነህ እየተባለ ተሰዷል፣ተገሏልም:: የአብን መወለድም ከዚሁ ጋር የተያያዘ እንደሆነ የድርጅቱ የተቋም ሊቀመንበር የነበሩት ዶ/ር ደሳለኝ ጫኔ በተደጋጋሚ አስርድተዋል:: ዛም ይህ ሁሉ መከራ እየደረሰበት በአማራነት እንዲደራጅ ቀርቶ እንዲጠራም አይፈልጉም:: ዋና ዳይሬክተሩ በመግለጫቸው በቅርቡ በቤኒሻንጉል ክልል እና በደቡብ ክልል ጉራ ፈረዳ ወረዳ ላይ ህዝባችን ላይ ትልቅ ጥቃት እና ግድያ ተፈፀሟል:: ይሁን እንጅ ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት እና የፀጥታ ሀይሉ ትልቅ ርብርብ እያደረገ እና ችግሩን እያስወገደ ይገኛል፤ ብለዋል:: ይህ ፅሁፍ እየተዘጋጀ በለበት ቦታ እንጓን ተወግዷል ያሉት ችግር በአፋር፣ በወሊጋና በጉራፍርዳ አማራው በማንነቱ እየተመረጠ መገደሉ አላቆመም:: መግለጫና አሽባሪነት የማይሰለቸው ብአዴንም በውሸቱ ቀጥሏል::

የክልሉ ኮሚኒኬሽን ዳይሬክተሩ ይኸን ጠቅሰው ነው እንግዲህ በእለተ ረቡዕ በ18/02/2013 ዓ.ም አማራው በየአካባቢው የሚደርስበትን ጥቃት ለማውገዝ በሚል ሰላማዊ ሰልፉ በማህበራዊ ሚዲያ መጠራቱን እና እየተቀሰቀሰ መሆኑን በመመልከት ኃላፊነቱን በሙሉ ፈልጎት ወስዶ ባስተባበረው ነበር በማለት ሰልፉ ህጋዊ ባለመሆኑና በክልሉ ማድረግ እንደማቻል ገልፀዋል::” ሰልፉን ሲከለክሉ ዋና ዳይሬክተሩ በምክንያትነት ያስቀመጡት...... “አሁን የሰብል ምርት በአንበጣ መንጋ የተወረረበት እና ሙሉ ትኩረታችንን የአርሶአደሩን ሰብል መታደግ ላይ እንድናውል በማስብ፣ ሁለተኛው የህዳሴ ግድቡን አስመልክቶ በሀገራችን ትልቅ አደጅዳ ስለሆነና ይህንን ተከተሎ በሰላማዊ ሰልፉ ሰበብ የአማራ ክልል እንዲረጋጋ ለማይፈልጉ ኃይሎች ሁከትና ብጥብጥ ለመፍጠር የሚመች በመሆኑ ሰልፍ አይፈቀድም በማለት ጠቅሰው ጠቅሰ” ይህን ተላልፎ ሰላማዊ ሰልፍ የሚወጣ አካል ግን ፖሊስ እና አጠቃላ የፀጥታ ኃይሉ እርምጃ ይወስዳል በማት ዝተዋል::

## አብን የጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ መንግሥት መከልከሉን ተከትሎ ታዋቂ ሰዎች ምን አሉ?

የአማራው ብሄረሰብ ተለይቶ በየቦታው የሚደርስበትን አሰቃቂ ግድያ ለማውገዝና ባስቸኳይ እንዲቆም ለመጠየቅ አብን ደጋፊዎቹን፣ አባላቱንና መላው ይህ ሃይ ባይ ያጣው ሰቆቃ የሚያሳስባቸው አካላትን በሙሉ በማስተባበር ጥቅምት 18/02/2013 ዓ.ም በአማራ ክልል እንዲሁም ጥቅምት 22/02/2013 ዓ.ም በአዲስ አበባ የጠራው ሰላማዊ ሰልፍ በመንግሥት መከልከሉና በህዝቡ ጥቃቱን ማስቆም ባለመቻሉ በታዋቂ ሰዎች፣ በምሁራን በሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና ድርጅቶች ከፍተኛ ውግዘትን ለስተ

### አርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነ፡ -

“ለእነዚህ ሁሉ ንፀሀን ዜጎች በየሳምንት መታረዱ፣ ሀብት መውደም፣ ነፃነት ማጣትና የመሳቀቅ ህይወት ምክንያቱ ምንድን ነው? የዚህ ሁሉ መከራ ምንጭ “ህገ መንግስቱ” ነው::” ይሄን የመከራ ምንጭ የሆነውን ህገ መንግሥት ታግለን ካልቀየርን በስተቀር ለቅሷችን ይቀጥላል::

ከመጮህ ይልቅ መሬት ላይ ወርደን ህዝቡን አደራጀተን ዘለቂ ነፃነትና እኩል ዜጋ አድርጎ የሚቆጥረንን ህገ መንግሥት ለማምጣት እንታገል::” የሚል መልእክቱን ቀደም ቡሎ በመንደርደሪያነት በማስደመጥ፤ የሚከተለውን ወግዘት አኑሯል::

ይድረስ ለአማራ ክልል መንግሥት ና አመራሮች፣ ለህይወቱ ዋስትና የሚሰጥ ላጣው የአማራ ሕዝብ ህይወቱን መታደግ ባትችሉ እንኳን እንዴት ሀዘኑን እንዳይገልፅ ትከለክሉታላችሁ? በስሙ እየኖራችሁ፣ ሲሆን መዋቅራችሁን ተጠቅማችሁ ስልፉን በመላው ኢትዮጵያ በማድረግ “አማራን ማሳደድ ይቁም” ማት ሲገባችሁ ጭራሽ ብሶቱን እንዳይናር መከልከል? ካለፈው የተማራችሁ መስሎን እንጅ ያለፈውን ረስተነው አይደለም::

### አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን፡ -

“በቅድሚያ የከብር ሰላምታዬን እያቀረብኩ በተለያዩ ሀገራችን ክፍሎች በተደጋጋሚ ጊዜ ዜጎች ላይ አላግባብ የሚፈፀሙ ኢ- ሰብዓዊና ማንነትን መሠረት ያደረጉ የማያበሩ ጥቃቶች ከቀርብ ጊዜ ወዲህ እጅግ ባልተገባ መንገድ ተስፋፋተው መቀጠላቸውን ተያይዞ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት በዋነነት መጠበቅያለበትና ይህ ጉዳ በቀጥታ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ጉዳዩ አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥቶ አገባብ ያለው መንግስታዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣና መስል ጥቃቶችን ዳግመኛ እንዳይፈፀሙ የሚጠብቅበትን በቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ በጥብቅ ማሳሰብ እወዳለሁ::

በዚህ አጋጣሚ በእነዚህ ጥያቂዎች ህይወታቸውን ላጡ ወገኖች ፈጣሪ ነብሳቸውን እንዲምር እና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መፅናናትን እንዲሆንለቸው ከልብ እመኛሁ::

ፍቅር ያሸንፋል!

ቴዎድሮስ ካሳሁን

(ቴዲ አፍሮ)

### ድምፃዊ ፋሲል ደሞዝ፡ -

“አማራው በየቦታው መሞት ቀጥሏል:: ከኢንጅነር ስመኘው በቀለ ግድ ጀምሮ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ አሁን ደግሞ በቤኒሻንጊል ሲሞትና ሲፈናቀል እያያችሁ እናንተ በአዴኖች ዝም ነው ያላችሁት:: ሆዳሞች ናቸው:: እድሜ ልካችሁን ተላላኪዎች ናችሁ:: እናንተ ነቀርሳዎች፤ ትልቁን የአማራ ሕዝብ አትወክሉም:: ድሮ ጀምሮ እናውቸኋለን፤ከአቶ አያሌው ጉበዜ በስተቀር ሌሎችን ጠንቅቀን እናዋቃችኋለን:: ታምራት ላይኔ፣ አዲሱ ለገሰ፣ በረከት ስምዖን አገኘሁ ተሸገር ጨምሮ የአማራን ሕዝብ ስነ ልቦና ያልተረዱ፤ እንዲያውም ያልሆኑ ተላላኪ አሽከሮች እንደነበሩ የማይካድ ሀቅ ነው:: ስለዚህ በቃ ተውት ህዝቡን ልቀቁት የአማራ ሕዝብ መሪ አያስፈልገውም:: ከጥንት ጀምሮ ይዞ በመጣው አኩሪ ባህላዊ ስርዓቱን ተከትሎ በየስፈሩ የጎበዝ አለቃ በመምረጥ አራሱን ያስተዳድራል” እንዲያውም አማራን ያለቀፈ ኢትዮጵያዊነት ገደል ይግባ” ሲል አውግዟል::

### የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ኦቦንግ ሜቶ፡ -

“ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በቤኒሻንጉል ከጉራ ፈርዳ ጨምሮ የሚደርሰውን ማንነት ተኮር ጥቃት በፅኑ አወግዛለሁ:: እጅግ ልብ ሰባሪም ነው:: አማራው አይደለም ሰልፍ ሰይፍ ቢያነሳ ከዚህ በኋላ አይፈረድበትም” በማለት ቅሬታቸውን ገልጿል::

## አርቲስት ይሁኔ በላይ፡-

"ይድረስ ለክልሉ መንግሥት

እንደፍርሃት እንዳትቆጥሩት!

ይህ ሕዝብ ሰላም ወዳድ አስዳማሚ ሰሚ ሕዝብ ነው! አሁን ተራው የመንግሥት ነው ! ድምፁን ስሙት በማንነታቸው ለሚገደሉ ንፁሃን ወገኖች ድረሱላቸው። ስርዓት የማስከበር ኃላፊነታችሁን ተወጡ ሀገሬ ፍቅርን ሰላምሽ ይብዛ!

ለዘለዓለም ኑሪልን!

ይሁኔ በላይ

## ዶ/ር ደረጀ ከበደ (ዘማሪ)፡-

"ሰላማዊ ሰልፍን ከለከለ" ከበስተጀርባው የአብይ አህመድ እጅ አለበት። ዴሞክራሲ ለውጥ ካለ የምትሉ ሰዎች ልዩነታችሁን አሳዩዋ! አማራ ግን ከተማዊ ስልፍህን ወጣ!

ድሉ የእግዚአብሔር ነው!! በማለት ከስልፍ ከልክለው ጎን ለጎን ጥሪውን ከማቅረብ ተቃዋሚውን አሰምቷል።

## በውቀቱ ስዩም፡-

"ከጥንት እስከዛሬ ሰወርድ ሊወራረድ የደረሰ መንግስታዊ ልማድ አለ፤ ጌቶቹ ሰርቶ አደሩን ሕዝብን ይበድላሉ! ከዚያ ደግሞ ለቅሶ መቀመጥን ይከለክላሉ፤ "እየየም ሲደላ ነው" የሚለው ያለምክንየት አይደለም! እየየም እንደልብ የማይገኝ ልዩ መብት ሆኖ ቆይቷል! ለማንኛውም ዜጎች ብሶታቸውን በሰላማዊ ሰልፍ ፀሐይ እንደመሞቅ ያለ ተፈጥሯዊ መብት እንጂ መንግሥት የሚሰጠውና የሚነሳው ነገር አይደለም። የባለስልጣች ድርሻ ሰላማዊ ሰልፈኞች በሰላም ወጥጠው በሰላም እንዲገቡ ማድረግ፤ ቅሬታቸውን እህ ብሎ ማድመጥና መፍትሄ መፈለግ ነው! ከታሪክ እንማር! "ኑ እንዋቀስ" እንጂ "ኑ እንቧቀስ" የሚል መንግሥት መቸም አያዋጣውም!

በውቀቱ ስዩም

## ኢ/ር ይልቃል ጌትነት፡-

"ትግስትም ልክ አለው"

የተጠራው ሰልፍ ዴሞክራሲን በማወደስ ወይም አማራጭ ፓለቲካ ሃሳብን ለሕዝብ ለማስተዋወቅ አይደለም። የሰልፉ አላማ ለዘመናት ሁሉ አይተን የማናውቀው የዘር ፍጅት በማያባራ መልኩ በአማራ ሕዝብ ላይ እየዘነበበት በመሆኑ ይህንን ለማስቆምና የትግሩ ምንጭ የሆነውን ዘረኛ ህገ መንግሥት እንዲቀየር መንገዶችን ለማመቻች ነው።

በታሪካችን እንደማናውቀ አማራ በሰው መሳ አውሬዎች የሚታረደውና ጥቃት የሚፈፀምበት በጨዋነቱና በህገ አክብሪነቱ ምክንያት ነው። ሁሉም በለጌና ጨዋ ሲደ ባለጌ የሚያሸንፈውን በጨዋው ህግ ከአክባሪነትና በበለጌው ስድነት ምክንያት ነው። ስለሆነም ከባለጌዎች ጋር የሚደረገን ትግል ለመመከት የባለጌዎችን ስነ ልቦናና አስተሳሰብ የሚመጥን መሆን አለበት።

## አርቴክ ዩሀንስ መኮነን፡-

"ባለ ሀይፍን ትቶ ባለ ሰልፍን?

እንስሳና እፅዋት እንኳን ለመብታቸው ተቆርቋሪ ቡድኖች በምሉባት ዓለም እየኖርን ሀገር አማን ብለው የሚኖሩ ንፁሀን ዜጎች ላይ የሚደርስን ጭማኔ የተሞላበት ግድ እና ማስገደድ ለማወገዝ የአንድ ፓርቲ ውይንም የተለያየ ብሄር አባል መሆን አያስፈልግም። ሰው ሆኖ መፈጠር ብቻ በቂ ነበር።

ከበረታችሁ ባለሰልፎቹን ሳይሆን ባለ ሰይፎቹን ከልክሉልን!

## ዶ/ር መኮንን ብሩ ( የሸዋ ኦሮሞ)፡-

"ፊንፊኔ ኬኛ ብሎ ሰልፍ የሚጠራ ጠባብ በሚርመሰመስበት ሀገር አማራ ላይ ያነጣጠረ ግድያ ይቁም ብሎ ሰልፍ መውጣት ወንጀል ሊሆን አይችልም። ወደድንም ጠላንም ለምንወዳት ኢትዮጵያ አማራን የአንበሳነት ደርሻ አማራ ላይ ማሴር ውለታ ቢስ መሆን ነው።

ዶ/ር መኮንን ብሩ

(የሸዋ ኦሮሞ በሀገር አሜሪካ የሚኖር)

ዶ/ር ተድላ ወ/ዮሀንስ (ወላይታ ተወላጅ)

"የአማራውን ሕዝብ ሰላማዊ ትግል አንድም ቀን ሳያቋርጥ፣ የአማራው ሕዝብ እንደ ሰው በሀገሩ በሰላም የመኖር ዋስትናው እስከመረጋገጥ መቀጠል ያገባዋል። እኔም እንደ አንድ ሰውና ኢትዮጵያዊ ከጎናችሁ ነኝ። የማንም ዘር የማንንም ዘር በዘሩ ተደራጅቶ መግዛት አይችልም።፤

## ሙክታር ኡስማን (የህግ መምህርና አክቲቪስት)

"አብን የወገንን ጭፍጨፋ በሰልፍ በመቃዎም ችግሩ ምንድን ነው? በሰልፍ ለውጥ አይመጣም በማለት ህግ መንግስታዊ መብትን ማገድ እንዴት ይቻላል? በቶርጅ ፍሎይድምት አሜሪካ እና መላው ዓለም በሰልፍ ተቃውመ አማራ በማንነቱ ሲጨፈጨፍ ቢቻል ሁሉ ኢትዮጵያዊ መቃወም ነበረበት ብላችሁ ለህዝቡ እንደመቆርቆ ጭራሽ ሰልፍ ታግዳላችሁ ጉዶች ናቸው።

## ዶ/ር ሙሳ ኮንቴ (ከአፋር ብሄራዊ ፓርቲ)

"በአማራ ወገኖቻቸው ላይ እየደረሰ ያለው ለይቶ የማጥቃት ዘመቻ አሁን ከአሁን እልባት ያገኛል በማለት "ልቤ እየደማ በዝምታ ቆይቻለሁ አሁን ግን በቃን! መንግሥት ውሎ ሳያድር መፍትሄ እንዲሰጥ በጥብቅ አሳስባለሁ"

ፖርቲዎችና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት

ባልደራስ፡-

"የዜጎችን መሰረታዊ መብት ማገድ ሰፊው ሕዝብ ሌሎች የመብት ማስከበሪያ ቢሮችን እንዲያንኳኩ መግፋት መሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## ኢዜማ

"ዜጎች ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ህገ- መንግስታዊ መብታቸው ሊከበር ይገባል ብሎ ያምናል። የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን) በአማራ ክልል ከተሞችና በአዲስ አበባ ከተማ ዜጎች ደምፃቸውን እንዲያሰሙ ሰላማዊ ሰልፍ ጠርቶ መንግሥት መከልከሉ ይታወቃል። ይህ መንግሥት ራሱን ፍራጅና ከልካይ አድርጎ ይህን መብት ጣሱ አግባብ አይደለም።

## አምነስቲ ኢንተርናሽናል (የሰብዓዊ መብት ተቋም)

"የኢትዮጵያ በባለስልጣናት ሊካሄድ የነበረውን ተቃውሞ ማፈናቸው ህገ- ወጥ እና አላስፈላጊ ነው" በኢትዮጵያ ለባለስልጣናት ሊደረግ የነበረው የተቃውሞ ጥሪ ታፍኗል። በኢትዮጵያ በሚደረገው ብሄር ተኮር ጥቃት ምክንያት ዜጎች በየጊዜው ይሞታሉ። ይህን ተከትሎ መንግሥት የዜጎች በህይወት የመኖር መብት ሊያረጋግጥ ይገባል። በሚል ሲካሄድ የነበረው ▶

# አኬልዳማዋ ኢትዮጵያ



ውቤ ደነቀው መኮንን

ትሕነግ/ኢሕአዴግ ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያ ሀገራችንን ሊበላትና ሊበታትናት ሲሠራ ቆይቷል። ሲያስገነግል ውድ ታጋይ ልጆቿንም ቁም ስቅል ሲያሳይ የነበረው ይህ ቡድን በቆራጥ፣ ግንባራቸውንና ደረታቸውን ለሀገር ሲሉ ራሳቸውን ለጥይት የሰጡት ጀግና ከሕዝብ አብራክ የተገኙ የእማ ኢትዮጵያ ውድ ፍሬዎች በከፈሉት የህይዎትና የአካል መስዋዕትነት የተገረሰሰው ነውረኛና ሆዳም ቡድንን ተከላከልኩ ብሎ አዲስ ለመጣውና ኢትዮጵያን ወደ ሰላምና ዴሞክራሲ ይወስዳል ተብሎ የተገመተው ራሱን የለውጥ ኃይል ብሎ የሰየመው ቡድን ወደ ሥልጣን ሲመጣ የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ ጨምሮ የብዙዎቻችን ደስታ እጥፍ ድርብ አድርጎት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ይህ ኃይል ወደ ስልጣን ማማው በሚወጣበት ጊዜ ቲም ለማ ይባል፤ ቲም ገዱ ወይም ቲም ደመቀ፤ ዞሮ ዞሮ በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ግምት ከ90% (ዘጠና እጅ ከመቶው) በላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታና ድጋፍ ያገኘ እንደነበር የሚታወቅ እውነታ ነው።

ተረኛው ኃይል ወደ ሥልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የቡድኑ አምበል የሚያደርጓቸው የታሰበባቸው (calculated) ንግግሮች ለብዙዎች መሸንገል ምክንያቶች ነበሩ። አሁንም እየተሸነገሉ ያሉ መኖራቸው ደግሞ ቡድኑ እስካሁን ካደረሳቸው የዜጎች ግድያ፣ መፈናቀል፣ መታገትና መሰል ችግሮች በበለጠ ወደ ፊት የሚመጣውን ችግርም አሳሳቢ ያደርገዋል። እዚህ ላይ የአቶ ሽመልስ አብዲሳን የማደናገር ወይም ማሳመን (Confuse or Convince) አባባል ማሰብ የነገሮችን አካሄድ ግልጽ ያደርግልናል። ለህዝባዊው ድጋፍ ምክንያት የነበሩትና ከተደረገው ዲስኩር አንጻር በሕዝብ ዘንድ ይፈፀሙልናል ተብለው ተስፋ ከተጣለባቸው ውስጥ፡-

1. ከፋፋዩን፣ በታኙንና አፍራሹን የሀገሪቱ የበላይ ህግ ህገ መንግሥት ተብዬው የጠላት ማኒፌስቶና አንድን ቋንቋ ተናጋሪን በሙሉ ለማጥፋት በሰው ባላዎቹ በትህነግና በኦነግ የተዘጋጀው እድሜው አጭር በሌላ ህዝባዊ ህገ መንግሥት ይተካል በሚል ተስፋ
2. የፌዴራል መንግሥቱ አወቃቀር ቋንቋንና ዘርን ምርኩዝ ባደረገና በሕዝብ ምርጫና ፍላጎት መሠረት አዲስ የፌደራል መንግሥት አወቃቀር ተግባራዊ እንደሚደረግ ተስፋ በማድረግ፣
3. ከላይ ይደረጋሉ ተብለው የታሰቡ ለውጦችን መሠረት በማድረግ ነፃ፣ ተአማኒና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ያከበረ ምርጫ ይካሄዳል ተብሎ ስለታመነ፣
4. ለዚህ ለተከናወነው ለውጥ በዋነኛነት ቀስቃሽና አቀጣጣይ የትግል ስልት በነበረው የማንነትና የውክልን ጥያቄዎች በአስቸኳይ እንደሚፈቱና ፍትሀዊ የውሳኔ እልባት እንደሚያገኙ በእርግጠኝነት በመተማመንና በአጠቃላይ ተግባራዊ ይደረጉ የነበሩት ፀረ ሕዝብና ፀረ ዴሞክራሲ የሆኑት ህጎች ተወግደው ለመጨረሻ የተገረሰሱና ተመልሰው እንደማይተገበሩ በመተማመን ለአዲሱ የለውጥ ኃይል ነኝ ላለው መንግሥት ሙሉ ድጋፍ ተቸሮት እንደነበር ሁላችንም በህሊናችን የቀረ የትናንት እውነት ነው።

በአንድ ሀገር የመንግሥት ለውጥ አስፈላጊ ሆኖ በሚከናወን ጊዜ ታግሎና መስዋዕትነት ከፍሎ ለውጡን ያመጣው ሕዝብ ይሁንታውን የሚሰጠው መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ መሆን ያለበት የሀገሩን ዳር ድንበርም የህዝቡን የዕለት ከእለት የፀጥታ ጉዳይ ማረጋገጫ ለነገ የማይባል ግዴታው እንደሆነ የታመነና ለአለማቀፋዊ እውነታ መሆኑ አስረጅ አያስፈልገውም።

በዚህ አኳያ ሲታኝ በመጀመሪያዎቹ የለውጥ ወራት በሀገራችን የሆነው ሁሉ ድንቅ ይመስል ነበር። የሀገራችንን ውስጣዊ ሰላም ለማረጋገጥና ከውጭ ሊመጡ የሚችሉ በጎ ያልሆኑ ተጽዕኖዎችን ለማስቀረት ያለመ በሚመስል መልኩ ያኮረፈና የትጥቅ ትግል መሰል ትግል እናካሄዳለን የሚሉትን ኃይላት ከግለሰብ ጀምሮ እስከ አነስተኛና ከፍተኛ ቡድኖች ከያሉበት ጠርቶና ኤርትራ ድረስ የልዑካን ቡድን በመላክ ወደ ሀገር ቤት አስመጥቷል። ሁሉም ግለሰቦች፣ ልዩነት አለኝ ብሎ በሀገሩ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ቡድንና የፖለቲካ ድርጅት ቀጣዩን ትግል በሀገር ውስጥ በመሆን ሰላማዊና የአስተሳሰብ ትግል በማድረግ ብቻ ወደ ተፈለገበት አላማና ግብ መድረስ እንደሚቻልና የብረት ትግሉን አስወግደን ሀገራችን ኢትዮጵያን ሌሎች የለሙ ሀገራት ከደረሱበት የእድገት ደረጃ ለማድረስ እንድንተጋ ጥሪ ተላልፎ ከጎረቤት ሀገሮችም ጋር ፍፁም ሰላማዊና ትብብር የተሞላበት ግንኙነት ይኖረን ዘንድ አዲስ የተሰየመው የአብይ አህመድ መንግሥት ትጋትን ያሳዩ ይመስል ስለነበር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሕዝብ ድጋፍ አልተለያቸውም ነበር።

## ሕልም እልም፤ ሕልም እልም!

አበው ጉድና ጅራት ከወደኋላ ነው እንዲሉ፣ የሰላሙን ጥሪ ተቀብለው ትጥቃቸውን ፈተው (እዚህ ላይ ትጥቅ ሳይፈቱም ከእነመሳሪያቸው የገቡም እንዳሉ ይታወቃል) ወደ ሀገር የገቡ በፊቱ የትህነግ/ ኢህአዴግ መንግሥት (ወሮ በላ ቡድን) ተቃዋሚ ነን የሚሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ወደ ሀገር ቤት በደማቅ አቀባበል (እንዳንዶቹ እጅግ በተጋነነ የአቀባበል መስተንግዶ ጭምር ከገቡ በኋላ ግማሽ እንደ እንጀራ ልጅ ባለእጁን ጋባዥነትና ከፋይነት በባለ አምስት ኮከብ ሆቴል እንደሚንፈላሰሰ መስማታችን ሳያንሰን ይኼው የባለ አምስት ኮከብ ሆቴል ቅምጥል በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ የመንግሥትን ስልጣን እቆጣጠራለሁ በሚል ቀቢፀ ተስፋ ምዕራብ ኢትዮጵያን የጦር አውድማ በማድረግ ከ20 (ሀያ) ያላነሱ የሕዝብና የመንግሥት ባንኮችን ያለማንም ከልካይና የተፈቀደ በሚመስል ውንብድና ዘረፈ። አስዘረፈ።

የሀገር ያለህ፣ የመንግሥት ያለህ!!! ተባለ። በወቅቱ ደራሽ አልነበረም ብቻ ላይን ሀይ ባይ በመጥፋቱ ያላስፈለገና ዘግናኝ አካል፣ የህይወትና የንብረት ውድመት መስዋዕትነት የምዕራብ ኢትዮጵያ ልጆች ከፈሉ። ቁሱም ዝም መድሐፉም ዝም ሆነና ታለፈ የተረኝነቱ የመጀመሪ መጀመሪያ አትሉም?

ይህ ከሆነ ከጥቂት ወራት ቆይታ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ በስተምዕራብ አቅጣጫ በሚገኘውና ቡራዩ ተብሎ በሚጠራው የከተማይቱ ክፍል ብሔርን በመሠረት ያደረገ ጭፍጨፋ፣ እርድና የንብረት ውድመት እቃን በመሰባበር፣ማቃጠልና መዝረፍን ጨምሮ ሊካሄድ ያስተዋሉ የመሀል አዲስ አበባ ወጣቶች ድርጊቱን በመቃወም በሰላማዊ መንገድ ▶

ለሕዝብና ለመንግሥት ለማሳወቅ ሰልፍ ለወጡ ንፁሃን ወጣቶች ተመጣጣኝ ያልሆነ የአፀፋ እርምጃ ግድያን ጨምሮ የተወሰደ ሲሆን ለእስር የተዳረጉት ወጣቶች እስከአሁን ድረስ በእርስ እየማቀቁ እንደሆነ ይነገራል።

ከዚህ ከቡራዩ እልቂት ጀርባ ከነበሩት የሥውርና ረጅም እጃቸውን ካስገቡት የፅንፈኛ ቄሮ አባላት በተጨማሪ የፅንፈኛ ቄሮ አምበልና አዛዥ የአል ሐጂ በደል በካይ ወራሽ አልሐጂ ጀዋር መሀመድ እንደሆነ ቢታወቅም አሁንም ቂሱም መጽሐፉም ዝም ሆነላችሁ! ተረኝነት ቁጥር ሁለት አትሉም ጎበዝ?

ከዚህ የቡራዩ የእልቂትና ማንነት መር የጅምላ ጭፍጨፋ ጥቂት ወራት ቆይቶ የፅንፈኛው ቄሮ አምበል ጀዋር መሐመድ ጥቃቶቹን አፏፋመ። የደቡቧ ፈርጥ ወደ ሆነችው ውቧ አምባ (ሀዋሳ ጎራ ብሎ የኢጄቶም አምባል እኔው ነኝ በሚል መንፈስ እናንተ የክልልነት ጥያቄአችሁን አፋፍማችሁ ቀጥሉ መልስ ካላገኛችሁ በኃይል በመጠቀም ክልል እናደርጋችኋለን እናም ለ11/11/11 ቀጠሮ ሰጡና እስከዚያው የክልልነት ጥያቄአቸው ካልተፈፀም ጉድ ይወለዳል ብሎ ቀጭን ትዕዛዝ አስተላልፎ መጣ።

ውድ እንባቢያን እደምታስታውሱት በ11/11/11 የተወለደው ከጉድም በላይ ነበር በዝርያ ሲዳማ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን እየተፈለጉና እየታደኑ በሀዋሳ ብቻ ላይሆን በአጎራባች ወረዳዎች ተጨፈጨፉ፣ በቤት ውስጥ እንዳሉ ሕፃናትና አረጋዊያን ሳይቀሩ ከነነፍሳቸው በእሳት እንዲጋፉ ተፈረደባቸው። ሀብት ንብረታቸው ወደመ የተረፈውም ያለማንም ከልካይ ተዘረፈ አካላቸው ተጎድቶ ከሞት ያመለጡትም ተሰደዱ ተፈናቃይና ለማኝ እንዲሆኑ ተደረጉ።

ከሀዋሳው ሰቆቃ በግምት ከ3 ወራት በኋላ ለሚከበረው የኢረቻ በዓል አከባበር ውትወታ የተጀመረ በጣም ቀደም ብሎ ሲሆን ቅስቀሳውም የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል ለየት የሚያደርገው ከአንድ መቶ ሀምሳ(150) ዓመታት በፊት አዲስ አበባ ከተማ እንዳይከበር ተከልክሎ የነበረ በመሆኑና ዘንድሮ "ፊንፊኔ" በአዲስ አበባ ከተማ የሚከበር መሆኑ አቦ ሽመልስ አብዲሳ እንደ ማስታወቂያ ሠራተኛ በተደጋጋሚና በተለያዩ ጊዜ በመናገር የስልጣናቸው ማዳበሪያ ያደረጉት ሲሆን ለማ መገርሳን በመተካት አዲስ ሹም ስለነበሩ የስልጣንና የመድረክ ሙቀቱን ግለቱን የተቋቋሙት አይመስሉም ነበር።

አይደረስ የለም የ2012 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልም ደረሰና ከዋዜማው ጀምሮ የመዲናችን የአዲስ አበባ አውራ ጎዳናዎች በትንሹ ከ5 ኪሎ ሜትር ራዲየስ (RADIOUS) ክርችም ተደርጎ የትራፊክ እንቅስቃሴ ከዜሮ በታች ሆኖ አደረ።

በዋዜማው የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ከካዛንቺስ አካባቢ እስከ መገናኛ ድረስ በትራንስፖርት እጦት መንገዱ በመዘጋቱም ምክንያት በእግር ጉዞ መሄዱን ያስታውሳል።

የበዓሉ እለት ማለትም የ2012 የኢሬቻ እለት ሀገሬ (አዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ) እቤቱ ቁጭ ብሎ በመዋል ሊከሰት ይችል የነበረውን ያላስፈላጊ ረብሻና ሊከፈል ይችል የነበረውን ያላስፈላጊ መስዋዕትነት በኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ትዕግስት ቁጭ ብሎ በመዋል ታላቅነቱን አስመስክሯል ጨዋውና ወገን ወዳጁ አዲስ አበቤ።

የሥልጣ ትኩሳቱን ያልቻሉትና ነፍጠኛንና ነፍጠኝነትን የክብረ በዓሉ ማድመቂያና ማጣፈጫ ያደረጉት አቦ ሽመልሽ አብዲሳ በበዓሉ ዋዜማ መቸም የማይረሳላቸውና ነውረኛውን ዲስኩራቸውን እንዲህ ሲሉ አቅራርተው ነበር።

አጠቅላለሁ "ከአንድ መቶ ሃምሳ ዓመት በፊት ተከልክሎ የነበረውን ኢሬቻን በዓል በፊንፊኔ ስናከብር በተሰበርንበት ቦታ ነፍጠኛን ሰባብረነዋል እንዲሁም 150 ዓመት በኋላ የሀገሪቱን መዲና ተቆጣጥረነዋል!! አሉልኝ ታላቅ ጦርነት ድል አድርጎ እንደገባ የጦር ጄኔራል።

ከዚህ በኋላማ አዲዮስ ዴሞክራሲ፣ አዲዮስ አንድነት፣ አዲዮስ መደመር ተረኝነቱ አፍጥጦና አግጥጦ የለውጥ ኃይሉ መመሪያ እንደሆነና የአንድነት፣ እኩልነት የመደመር ሰበካው የተረኝቱ ጭምብል መሆኑ በይፋ ተገልጦ የታዩበት ሆኖ አለፈ።

የአብይ አህመድ የመደመር የፎቶ ሾው ፍልስፍና ሆነ የፓርክ ግምባታ ጭምብል እንዲሁም የቲም ለማ የኦሮሚያ ሪፖብሊክን የመመሥረት ድብቅ አጀንዳ በአቦ ሽመልሽ የመድረክና የሥልጣን ሙቀት አለመቻልና መቃተት ራቁቱን ሆኖ ፀሐይ ይመታው ጀመረ።

የኢሬቻ በዓል አካባበር ሙቀት ሳይበርድ ምናልባትም ከአንድ ወር ባልበለጠ የጌዜ ርቀት ጉደኛ አጀንዳ ብቅ ያለ ሲሆን ይኸውም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ያሉትንና የተናገሩትን ሁሉ ያላንዳች ማንገራገርና ማወላወል ለሚቀበላቸው የትህነግ/ ኢህአዴግ ፓርላማ በመጠቀም ሀገራችን ለጉዳትና ለብጠብጥ ለሚዳርጉ ሰዎች ያለንት ትዕግስት አልቋል በዚህ የሚቀጥሉ ከሆነና ከእኩይ ድርጊታቸው የማይታቀቡ ከሆነ የማያዳግም ህጋዊ እርምጃ እንወስዳለን በማለት ካስጠነቀቁ በኋላ በማታው አውሮፕላን ወደ ሞስኮ እብስ አሉ ተባለና በማታው ዜና ሰማን።

ይህችን የጠቅላዩን ንግግር የሰማን ሁሉ ጎሽ ለካ ለካ ጠቅላይ ሚኒስትራችን በጣም ትዕግስተኛ ስለሆኑ ነው እስካሁን የሖነው ሁሉ ሊሆን ዝም ያሉት።

ከአሁን በኋላ OMN ሰይጣናዊ መልእክት የሚያስተላልፍና ሕዝብን ከሕዝብ ለማባላት የዘር ማጥፋት ቅስቀሳ የሚያካሄድ ጽንፈኛ ሚዲያ (ቴሌቪዥን ስርጭት ይዘጋል ወይም የዚሁ ሚዲያ ባለቤት ጀዋር መሐመድ የተባለው ሰይጣዊ ሰው አደብ ይገዛል በሚል የእፎይታ ስሜት ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላም ተስፋ ሰነቀ።

ጠቅላዩ በዚያው ለፓርላማቸው ንግግር ባሰሙበት ቀን ምሽት ላይ ወደ ሞስኮ (ሩሲያ) መብረራቸው ከተሰማ ከጥቂት ሰዓታት ቆይታ በኋላ ንጉሡ ነገሥት አልሃጂ ጀዋር በካሳ በፌስ ቡክ ገፁ ተከብቤአለሁ ጥበቃዬም ተነስቶብኛል ቶሎ ድረሱልኝ በማት ለመናጀ መንጋው በማስተላለፍ ኡኡታውን አቀለጠዋል!!!

ከዚህ በኋለ የሆነውና የተፈፀመው እውን ይኼ ነገር እየተደረገ ያለው በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ስም ነው ወይስ ሌላ ቦታ በማለት የታየውንና የሚታየውን የግፍ ተግባር ማመን እስኪያቅት ድረስ የሰው ልጅ በብሔርና በእምነቱ እየተመረጡ እንደ ከብት ታረደ፣ ጭንቅላቱ በመንጋ ድንጋይ ተፈጠፈጠ፣ በቤት ውስጥ እንዳለ ከውጭ ተዘግቶበት ከእነነፍሱ በእሳት ላንቃ እንደ ጧፍ ተንቀለቀለ፣ የሰው ልጅ አስከሬን እየተጎተተ ፎቶግራፍ መነሻና መሳለቂያ ተደረገ፣ ከ80 ዓመት እድሜ ታማሚ አልጋ ቁራኛ ሽማግሌ እስከ የአራት አመት እድሜ ህፃን ላይ የሰው ልጅ ለእርድ ቀረበ እጅግ ዘግናኝና አሳዛኝ ትዕይንት!!!

ከ3 እስከ 2 ተከታታይ ቀናት ይኸ ሰቆቃ ኦሮሚያ ተብሎ በተሰየመው በተለያዩ ቦታ ተከናውነ። ጀዋር መሐመድም ፎከረም አቅራራም በመጨረሻም አሁን ያለንን አቅም፣ ጉልበትና ኃይል አሳይተናል አቁሙ ብሎ መንጋውን አዘዘ። ንጉሡ ነገሥት ዘ- ቄሮ ወ- አራጅ አል ሃጂ ጃዋር መህመድ ያዘዘው ሁሉ ሆነ።

ስለዚህ የጀዋር መሐመድ በዘርና በእምነት ለይቶ ንፁሐን ኢትዮጵያዊያንን ማሳረዱና አቅምና ጉልበቱን ያላየበትን ሁኔታ በማድረቅና ደስታና አጋርነታቸውን ለመግለፅ

1. አቦ ሽመልስ አብዲሳን የቀደማቸው ያለ አይመስለኝም እሳቸውም አሉ፡- የጀዋር መሐመድን ጥበቃ ያነሳ በህግ ይጠየቃል ጀዋርን እንጠብቀዋለን እና ባስቸኳይ ጥበቃው እንዲመለስለት ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ ለማን? ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጄኔራል (ለፌዴራል ፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ) ይታያችሁ አንድ የክልል አስተዳደር የሐገሪቱን የፌዴራል ፓሊስ አዛዥ አሻቅበው ትእዛዝ ሲሰጡ ይህ እንግዲህ ከተረኝት እብሪት በስተቀር ሌላ ምን ሊባል ይችላል? "የድርጅቱ እናቲቱን አንቺ ልጅየውን አንቱ"
2. አቦ ደውድ ኢብሣ (የዛሬን አያድርገውና ሳይንሳፈፍ በፊት)
3. አቦ ብርጋዴር ጄኔራል ከማል ገልቹ እና ሌሎችም የተለያዩ ባለስልጣናት በኦሮሚያ የሚንቀሳቀሱ የፓርቲ መሪዎች የእንኳን ደስ አለህ የአጋርነት መግለጫ በህብረት በዚያው በጀዋር OMN TV አስተላለፉ ጉድ ተባለ!!!

ይኼ ሁሉ የግፍ ግፍ ሲፈፀም በመሪ የሚያምነውና በመሪውም ተስፋ ያልቆረጠው ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባውን እያነባም እያበሰም አንዳች ነገር ከጠቅላዩ ይጠብቅ ነበር እንዳው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን ሁሉ ጉድ አልሰሙ ይሆን? ለሞስኮ ጉብኝታቸውን

አቋርጠው ይመጡና ሀገር ያረጋጋሉ ተብሎ ቢጠበቁ እሳቸው ምን በወጣቸው ቀስ ብለው፣ ዘንጠው ፎቷቸውን ተነስተው ስብሰባቸውን ጨርሰው እንኳን የ86 ንፁሃን ዜጎች ህይወትና ንብረታቸው (ይሄ ቁጥርር መንግሥት ባመነው መሠረት እንደሆነ ልብ ይሏል) የጠፋበት ሀገር መሪ ሊመስሉ አንድ ሰባራ ሳንቲም የጠፋበትም ነጋዴም አልመሰሉ ያልተነካ ግልግል ያውቃል አይደል ወጉስ!!!

ከሞስኮ ከተመለሱም በኋላ ከዛሬ ነገ መግለጫ ይሰጣሉ በፓርላማቸውም ፊት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባለሙት ንግግርና ለጀዋር መሀመድ በሰጡት ማስጠንቀቂያ መሠረትም ጀዋርን በቁጥጥር ስር አውለው ለህግ ያቀርባሉ ተብለ ሲጠበቁ እሳቸው እቴ!!! ወይ ንክች ያባቢለዋ ልጅ!!!

ለካስ ጀዋር መሀመድ የተፈቀደለት ወንጀለኛና ኢትዮጵያ ሀገራችንን ለመበተን ቡራኬ የተሰጠው አካይስት ኖሯል ወገን?

በግምት ከሞስኮ ከተመለሱ (ጠቅላዩ ማለት ነው) ከ10 ቀናት በኋላ ይመስለኛል በማንነታቸውና በሚያራምዱት እምነት ምክንያት እየተለዩ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅና የመአከላዊ ኢትዮጵያ ለተጨፈጨፉ አስከሬኖች ብሔርን ቁጥር በመስጠት በጉጉት ይጠበቅ የነበረውን መሪያዊ መግለጫ ውሃ በመቸለስ አይነት ኩም ካደረጉን በኋላ የጃዋር መሐመድ መንጋ በዋንኛነት በሰዎች አካልና ህይዎት እንዲሁም በንብረት ማውደምና አቢያተክርስቲያናትን በማቃጠል አደጋ ከደረሰበት የሀገራችን ክፍል ወደ ሐረር ከአጋር ባለሥልጣናቻቸው ጋር በመሄድና ስብሰባ በመቀመጥ ጃዋር መሀመድ ወንድማችን ነው ለምን እንገለዋለን እስካሁን አብረን እየሠራን ነበር አሁንም አብረን እንሠራለን እንጠብቀውማለን በማለት ቢደሰኩሩልንና ጀዋር ኢስኮርታችን ነው ብለው ቁርጣችንን የነገሩንን በማሰብ ወደፊት የጨለማ ጊዜ እንደሚመጣና ትግሉ የመረረና የከረረ እንደሚሆን ነቢይ መሆን አላስፈለገንም ነበር።

ከዚያም ጊዜ በኋላና ያንን ሁኔታ ተከትሎ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተለይም በቤኒሻንጉል ክልል ማንነትን መሠረት ያደረጉ እርዶችና የሰው ልጅ ደረትና ጭንቅላት የቀስት ጦር ማነጣጠሪያ እስኪሆን ድረስ በቁጥር ለሚታክት ጊዜ በተደጋጋሚ የሰው ህይዎት ሲቀስፍ የከረመበት ሁኔታ የትናንት ትዝታ ሲሆን በተለይ ደግሞ ከዛሬ 1 ወር በፊት በሚሆን ጊዜ አቦ ሽመልስ አብዲሳና አቶ አሻድሊ ሀሰን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ርዕሰ መስተዳደርን የአማራ ክልል ባለሥልጣናት የክብር ካባ ብለው ከሸለሙ ምናልባትም ከሽልማቱ 15 ቀናት በኋላ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሚገኘው የመተከል ዞን (የቀድሞው ጎጃም ክፍለ ሀገር አንድ አውራጃ የነበረ መሆኑን ያጤናል) አስተዳደር አካላት በሆኑት የተለያዩ ወረዳዎች የአማራ/አገው ማንነት ባላቸው ነፃ በሆኑ የኢትዮጵያ ዜጎች ላይ በቀስት ወንጭፍና ዘመናዊ ትጥቅ በታጠቁ ወንበዴዎች ግድያ የንብረትና የቤት ቃጠሎ በተካሄደበት ወቅት የነፍሰጡር እናት ሆድ በሳንጃ ተቀዶ በማሕፀን ውስ የነበሩና ለመወለድ ጥቂት ጊዜ የሚቀራቸው ህፃናት ሜዳ ላይ ጫካ ውስጥ ተጥለው የታዩበትን ሁኔታ ወላድ ሁሉ ምን ሊል እንደሚችል ፍርዱን ለአንባቢ እተወዋለሁ።

እንግዲህ እኚህ የክልል አስተዳደር ናቸው ም/ጠቅላይ ሚኒስቴር ደመቀ መኮንን መተከል ከጎበኙ በኋላ ህብረተሰቡ መንግሥት ይደርስልናል ብሎ መጠበቅ የለበትም። ይልቅስ ራሱን አስታጥቆ አካባቢውንና ቤተሰቡን እንዲሁም ራሱን መከላከል ይገባዋል አሉ። አቶ አሻድሊ ሀሰን ይከፉም ይልማ የሀገሪቱን ም/ጠቅላይ ሚኒስትር ሲተቹ የም/ጠ/ሚ/ውን ንግግር ከአንድ ከማይረባ ሰው የሚጠበቅ ንግግር አይነት እንደሆነና እኛ ከፈለግን "እነ አቶ አሻድሊ ሀሰን" በአንድ ቀን ድምጥማጡን ነው የምናጠፋው ማንን? አማራውንና አገውን ስለዚህ ብንከባበር ይሻላል በሚል ዛቻ አቶ ደመቀን አሻቅበው ያስጠነቀቁበት ሁኔታ አሁንም የፍንጅርቱ እናቲቱን አንቺ ልጅየውን አንቱ" ብሄል እንድናነሳ ያስገድደናል።

ይህ በአንዲህ እንዳለፈና ምናልባትም ከዚህ ትዕይንት ቀደም ብሎ በሀገራችን በደቡብ ክፍል የሚገኘው የወላይታ ዞን የክልልነት ጥያቄ አንስቶ ተግባራዊነቱን ለማፍጠን የአደባባይ ተቃውሞና የጥያቄው መልስ ይፈጥን ዘንድ ሰልፍ በወጡ ዜጎች ላይ የግድያና የአካል ማጉደል ርምጃ የተወለደበት ሁኔታ ሳንዘነጋ አሁን በዚህ ወቅት የዚህ ጽሑፍ እራቢ የታዘባቸውን ነገሮች በሚከት ትብብር ሁኔታ አሁንም በሀገራችን ደቡብ በሚገኘው የጉራ ፈረዳ ወረዳ ማንነትን መሠረትና ምርኩዝ ያደረገ ከላይ በተጠቀሱት አረመኔያዊ የአገዳደል የጭካኔ ስልት በመጠቀም አካባቢውን የዞን ደረጃ ለመስጠት የሚፈልጉ የታጠቁ ኃይላት (ሽኮዎች) ይላቸዋል። ዜናው ንፁሐን ዜጎች እየተጨፈጨፉ ይገኛል።

መንግሥት እርምጃ ምን ይሆን? ይህን? የነፍስ አድን እርምጃ መውሰድ ይሆን? ወይስ አሁንም መጽሐፉም ዝም ቂሱም ዝም ይሉ ይሆን።

ስለዚህ ይህች ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ለሰላም ወዳዱ ህዝቧ ላይን ለአምባገነንና ጨፍጫፊ መሪዎችና ጀሌዎቻቸው የገፀ በረከት የተሰጠች ሀገር እስከምትመስል ድረስ የሚተካኩት መሪዎች ሁሉ በተለይም ከሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሰባት ዓ.ም (1967) ወዲህ በኢትዮጵያ የቅኝት መንበር ላይ ፊጥ ያሉ መሪዎ የኃይማኖት መሪዎ የማይገደዷቸው፣ ሚኒስትሮቻቸው ተቃውሞ የማያቀርቡባቸው ይልቅ እጅ በመንሳትና ሲያስነሳቸው ጭምር በማጨብጨብ በአምባገነንነት እብሪት እንዲያብጡ የሚያበረታቷቸው፣ በቅርብ ጓደኛ ምክር የማይሰማቸው ሲፈልጉ የሚበትኑት ሲፈልጉ የሚደምሩት ሕዝብና ሀገር ነው ለካ ያላቸው።

የካቢኔ ሚኒስትሮች የጠ/ሚው፣ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳልሆነ የጠርና የጠርና የፀጥታ ኃላፊዎችም እንዲሁ የሾሚ አለቃቸው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳልሆኑ ሁሉ ሕዝብ በዘፈቀደ በሚሰቀጥጥ ሁኔታ ተጨፍጭፎ ሲያልቅና የሀገር ሀብትና ንብረት ሲወድም፣ ሀገር መስራች ብቻ ሳትሆን በራሷ ሀገር የሆነችና የብዙ የሀገር ውለታዎች ባለቤት የሆነችው እናት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስትደፈር፣ ስትቃጠል ስትወድም ዝም ብሎ ባልታዘዝኩም አባዜ ቆሞ የመመልከት ነውር እየተሰራባት ያለች ምናልባትም ከአምላክ በስተቀር ባለቤት የሌላት ሀገርና የዓለም አቀፍ ማህበረሰብም በአላየሁም አልሰማሁም አውቆ አይን የመጨፈን ተንኮልና ይች ሀገር ከሊግ ኦፍ ኔሽንስ (League of Notiones) የመጀመሪያውና የከሸፈው እንዲሁም በኢትዮጵያ ምክንያት የፈረሰው የንጉሡ ነገሥቱ የድረሱልኝ ጥሪ ውድቅ ያደረገበትና በኢትዮጵያና በወራሪው ኢጣሊያ ላይ እኩል የመሣሪያ ሽያጭ ማዕቀብ የጣለበት ከህደት

በሁለተኛው ደረጃ በ1990 እ.ኢ.አ የኢትዮጵያ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ወራሪንና ተወራሪን በአንድ የተንኮል አይን በማየትና ኢትዮጵያ እንድትፈራርስ በእነኸርማን ኮሀን የተደረገብን አለማቀፋዊ ደባ ከዛሬ ሦስተኛው ደረጃ ከዛሬ ሦስት ዓመት ወዲህ፣ በዚህ ባለንበት ዘመንና በአሁኗ ሰዓት ጭምር ተከታዮችን እንዲሁም ቅድስት የተዋህዶ ቤተክርስቲንን ለይቶ ኢላማ በማድረግ በራሳችን መሪዎችና በጽንፈኞች ብሔርተኞች እየደረሰ ያለውን ስብአዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ውድመት ሊተባበሩት መንግሥት ጽ/ቤት ለተለያዩ ሰብዓዊ ጉዳይ ይመለከተናል ለሚሉ ዓለማቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና የሰላም ወዳዱ አለማቀፋዊ ህብረተሰብ በጀግናው የሕዝብ ልጅ ጋዜጠኛና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች በሆነው እንቁ ኢትዮጵያዊ በታላቁ እስክንድር ነጋ አማካኝነት ኢትዮጵያ ለመላው ዓለም ብታሳውቅም አሁንም በቸልታ በማዬትና እንደ ሩዋንዳ የሁቱና ቱትሲ ኢንተር ሀሞይ ፍጅት አስከሬን ሊቆጥሩ ይመጡ ይሆን? ከዚህ በፊት ለኢትዮጵያ የሚደርስላት የነገሥታት ንጉስ የአማልካቾች አምላክ ቸሩ መድኃኒያለም አይዘነጋትም አሁንም ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋና የህዝቧም እንባ ወደ አምላካቸው ጎርፍ ሆና ይፈስ ዘንድ ግድ የሚለን ጊዜ ላይ ነንና አምላካችን ይድረስልንና ፅናትና ጥንካሬውን ይቸረን ዘንድ ሁላችንም በአቋማችን እንፅና!!!

ንቁም በበህላዊነ እስከንረክቦ አምላክነ ያለውን የሊቀመላኩ ቅ/ገብርኤልን ጽናት ጥንካሬ ይስጠን።

ወስበሀት ለእግዚአብርሐር!

አሜን (3)

# የኢትዮጵያ ታሪክና የወደፊት የትግል አቅጣጫ . . .



አቻምየለህ ታምሩ

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጋሞው መነኩሴ በአባ ባሕርይ የተጻፈውን «ዜናሁ ለጋላ» ያነበበ ሁሉ ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ኦሮምያ በሚባለው ክልል ውስጥ ኦሮሞ ባልሆኑ ነገዶችና ኦሮሞ አትመስሉም በተባሉ ኢትዮጵያውያን ላይ እየተካሄደ ያለውን ፍጅት ተመልክቶ በአባ ባሕርይ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን ታሪክ ሲያስታውስ በሁለቱ ዘመናት መካከል ያለው ተመሳስሎ አራት መቶ ዓመትን ወደ ኋላ ተመልሶ ታሪኩ የተነገረበትን ዘመን የኖረ ያህል ስሜት ቢፈጠርበት አይፈረድበትም። የኦሮሞ የገዢ መደብ የሆነው ሉባ የጭካኔ ባሕል፣ የገዢ መደቡ ሉባ ለመሆን በሚያካሂደው የቦታ ጦርነት የሚፈጽመው አረመኔያዊ ጭካኔ ሁሉ ዛሬ ቄሮ ነን የሚሉ የጃዋር መሐመድ mindless መንጋዎች፣ የኦነግ ታጣቂዎች [ወታደሮች ላለማለት ነው] እና የኦሕዴድ ወታደሮች በጥምር ከሚያካሂዱት ጋር አንድ አይነት ነው።

ዐይናችን እያየ በወገናችን ላይ ሲፈጸም የምናዬው ጭካኔ ሁሉ ገዳ የሚባለው የኦሮሞ ገዢ መደብ ወታደራዊ ሥርዓት ተቋማዊ ያደረገው culture of violence ውጤት ነው። የገዳ ሥርዓት ከሌሎች ወታደራዊ ሥርዓቶች የሚለየው በምርኮኞች ላይ ሳይቀር ritualized የሆነው culture of violenceን ተቋማዊ ማድረጉ ነው። ሌሎች ወታደራዊ ሥርዓቶች ጠላት እንኳ ቢሆን የምርኮ አያያዝ ሥርዓት አላቸው። በገዳ ሥርዓት ግን ኦሮምኛ የማይናገር ሁሉ መጥፋት ያለበት ጠላት ነው።

በገዳ ሥርዓት በፊት የነበረው ሉባ ያልወረረውን ያልወረረ፣ ያላጠፋውን ያላጠፋ፣ ያልዘረፈውን ያልዘረፈ፣ ያላወደመውን ያላወደመ የሉባ መሪ ወይም አባገዳ መሆን አይችልም። ዛሬ ባገራችን የምናየው የኦሮሞ ያልሆነውን ማቃጠል፣ ማውደም፣ ሰላማዊ ሰውን በጭካኔ መግደል፣ ቤተክርስቲያን ማቃጠል፣ መዝረፍ፣ ወዘተ. . . ሁሉ የገዳ ሥርዓት ተቋማዊ ያደረገው የኦሮሞ የገዢ መደብ culture of violence ውጤት ነው።

እኔ በበኩሌ የጃዋር mindless መንጋ ኦሮሞ ባልሆነው ሕዝብ ላይ እያካሄደው ያለውን ጭካኔ ስመለከት አባ ባሕርይ በመጽሐፍ መልክ ትተውልን ያለፉትን ፊልም በዐይነ ሕሊናዬ የማየው ያህል ተሰምቶኛል። በመሆኑም ዛሬ እየተካሄደ ያለው ሁሉ የኦሮሞ የገዢ መደብ ወታደራዊ ሥርዓት የሆነው የገዳ ሥርዓት ተቋማዊ ያደረገው ritualized የሆነው culture of violence ውጤት ነው።

ባጭሩ ቄሮ የሚባለው የጃዋር መንጋ፣ የኦነግ ታጣቂዎችና የዐቢይ አሕመድ ወታደሮች በጥንቱ የኢትዮጵያ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ እያካሄዱት ያለው የዘር ማጥፋት ዘመቻ ባለፉት አራት መቶ ዓመታት የመጣንበትን የኢትዮጵያን ታሪክ በቅጡ ባለማወቃችን የፈጸምነው ሐጢያት እያስከፈለን ያለ ከፍተኛ ዋጋ ነው። የጥንቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰፋሪና መጤ እየተባለ በሕገ ወጥ ወራሪዎች የዘር ማጥፋት እየተካሄደበት ያለው አውሮፓውያን ላቲን አሜሪካንና አፍሪካን መወረር ከጀመሩ ከስንት ዘመናት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ሕገ ወጥ ወራሪዎች ነው።

ኢትዮጵያዊ አይደለንም እያሉ በኢትዮጵያ ምድር የተተከሉ የጸረ ፋሽስትና የጸረ ቅኝ ግዛት ምልክቶችና የኢትዮጵያና የአፍሪካ አባቶች የሆኑ ጀግኖችን ሐውልቶች ሲያፈርሱ፤ የገዳ ሥርዓት ተቋማዊ ባደረገው የኦሮሞ

የገገር መደብ culture of violence እየተመሩ አውዳሚ፣ አረመኔያዊና ጭካኔ የተሞላበት የዘር ማጥፋት ዘመቻ ሲያካሂዱ የሚውሉ ወራሪዎችን ማባበሉ ማብቃት አለበት።

የኢትዮጵያን ነባር ነገዶች እያጠፉ፣ ከርስታቸው እያፈለሱ፣ በሕይዎት የተረፉትን ገርባ [ባርያ] እያደረጉ፣ ቅርስ እያወደሙና ስልጣኔ እየደመሰሱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን ሕገ ወጥ ወራሪዎች ከነሱ በፊት አፍሪካንና ላቲን አሜሪካን የወረሩት አውሮፓውያን በወረራ የወሰዱትን ርስት ለባለቤቶቹ መልሰው ተነቃቅለው ከአፍሪካ ምድር እንደወጡ ሁሉ እነሱም ወደ አገራችን መጥተው ለፈጸሙት የዘር ማጥፋት፣ ላጠፏቸው ነገዶች፣ ለደመሰሱት ቅርስና ሥልጣኔ ሁሉ ተጠያቂ ሆነው በወረራ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ከርስታችን ላይ ላገኙት ጥቅም አፈላማ ከፍለው ርስቱን ለባለቤቱ መልሰው አገራችን ወደሚሉት ሊሄዱ እንደሚገባ ትግል መጀመር አለብን። ርስታችንን ሰጥተን አንድነት ማምጣት ካልቻልን ያለን የመጨረሻ አማራጭ እንደ ዋርካ የተንሰራፉበትን የአባቶቻችንን ርስት ለቀው ኦሮምያቸው ከባሌ በታች እንዲፈልጉ ማድረግ ብቻ ነው። ይህን በተፈጥሮ ሕግም በእግዚያብሔር ሕግም መሠረት አለው።

የደቡብ አፍሪካ ፓርላማ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ አገራቸው የገቡ ነጮች የወረሩትን የጥቁሮቹን መሬት ለቀው እንዲወጡ ሙሉ በሙሉ ወስኗል። ደቡብ አፍሪካ በደቾች የተያዘችበት ዘመን ኢትዮጵያም ከባሌ በታች በተነሱ በአባገዳ በሚመሩ ወራሪዎች የተወረረችበት ዘመን ነው። በተለይም የመጀመሪያዎቹ የአምስት አባገዳዎች ወረራ ማለትም የሜልባ፣ የሙደና፣ የኪሎሌ፣ የቢፎሌና የምስሌ ወረራ ደቾች ደቡብ አፍሪካን ከተወረሩበት ዘመን ጋር ይገጥማል።

የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተወረረውን ሥርታቸውን ዛሬ ካስመለሱ ደቾች ደቡብ አፍሪካን በወረሩት ዘመን በአባገዳ እየተመራ በተካሄደው ወረራ የተወረሩት ባሊ[የዛሬው ባሌ]፣ፈጠጋር [የዛሬው አርሲ]፣ ደዋሮ[የዛሬው ሐረርጌ]፣ እናሪያ [የዛሬው ኢሉባቦር]፣ ቢዛሞን [የዛሬ ወለጋን] ወደ ነባር ባለቤቶቹ ሊመልሱ የማይችሉበት ምድራዊ ምክንያት ሊኖር አይችልም። እንዴውም የደቡብ አፍሪካ ፓርላማ ውሳኔ የተወረረብንን የአባቶቻችንን ባድማ ለማስመለስ precedence set አድርጎልናል።

የአውሮፓዎቹ ጥንታዊ አገር ስፔንም ዜጎቿ የአገራቸው ባለቤት ሆነው በሰላም የሚኖሩት Reconquista ባሉት እንቅስቃሴ ወራሪዎቻቸው ለብዙ መቶ ዓመታት የወሰዱባቸውን ርስታቸውን አንድ በአንድ በማስመለስ ነው። እኛም Reconquista በማድረግ የተወረረብንን ርሥታችንን ማስመለስ አለብን። ይህንን በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ብቻ ሳይሆን በፈረንጆችም ቋንቋ በመጻፍ ታሪካችንን ዓለም እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርብናል።

በሰልፍም ሆነ በአቤቱታ በምናደርገው ትግልና በምንሰጠው ምላሽ ሁሉ በኢትዮጵያ እምብርት ላይ የበቀለው «ኦሮምያ» የሚባለው እባጭ አባገዳዎች በየስምንት ዓመቱ ከባሌ በታች ካለው አገራቸው ተነስተው ነባሮቹን የኢትዮጵያ ነገዶች ባገራቸው ላይ እያጠፉና ገባር እያደረጉ፤ የተጋፈጧቸውን ከርስታቸው እያፈለሱ፣ በትእዛዝ ማንነታቸውን እየቀየሩና የገነቡትን ስልጣኔ ሁሉ እያጠፉ እንደ ዋርካ ተስፋፍተው በወረራ የያዙት የአገራችን ክፍል እንጂ ኢትዮጵያ የራሷ ያልነበረን አንድ ኢንች የሰው መሬት ወርራ እንደማታውቅ መናገር አለብን።

የመለስ ዜናዊ አማካሪ የነበረው የሲ.አይ.ኤው ፓል ሄንዝ ስለኦነግና በአጠቃላይ የኦሮሞ ፖለቲካ ሰለተመሰረተበት የውሸት ታሪክ እንደጻፈው ኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉት ኦነጋውያን ያሻቸውን ሊቀረጹ ይችላሉ! ኦነጋውያንን ገና ጫካ ጀምሮ የሚያውቃቸው ፓል ሄንዝ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በኅምሌ 30 ቀን 1992 ለመለስ ዜናዊ በጻፈለት ረጅም ደብዳቤ ስለኦነጋውያን ተረት ተረት የሚቀጥለውን ጽፎ ነበር፤

“The OLF tries to represent the Oromo as victimized by Menelik and never given justice for their sufferings. They are entitled to their own view of their history, but they cannot require other Ethiopian peoples to accept it. Much of their history is selective mythology. They forget that in historical terms, the Oromo are one of the newest [underlined in the original] peoples in Ethiopia. Europeans in North America and whites in South Africa have occupied their territories longer than the Oromo in most regions of Ethiopia.”

ትርጉም፤

“ኦነግ ኦሮሞን በምኒልክ የተጠቃና ለደረሰበትም ጥቃት ፍትህ ያላገኘ አስመስሎ ለማቅረብ ይጥራል። ስለታሪካቸው የራሳቸውን አመለካከት ሊኖራቸው መብታቸው ነው፤ ነገር ግን ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦችን እንዲቀበሉት መጠየቅ አይችሉም። አብዛኛዎቹ ታሪካቸው የተመረጠ ተረት ነው። በታሪክ በነባርነት አንጻር ኦሮሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ነገዶች ሁሉ በጣም አዲስ መጤ (ገብ) ሕዝብ መሆኑን ረስተውታል። አውሮፓውያን ወደ ሰሜን አሜሪካ እና ነጮች ወደ ደቡብ አፍሪካ የገቡበት ጊዜ ኦሮሞዎች በአብዛኛው የኢትዮጵያ አውርጃዎች ከሰፈሩበት ጊዜ ይረዝማል።”

ፖል ሄንዝ እንዳለው ኦነጋውያን ተረት ተረት እየፈጠሩ ታሪክ ነው በማለት ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ኦሮሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖር ነበር፣ ኦሮሞ ነባር ሕዝብ ነው እያሉ የሌለ ልብ ወለድ የሚፈጥሩበት ምክንያት ሕዝባችን የሚሉት የሰፈረበት ምድር የሌሎች ኢትዮጵያውያን አጽመ ርስት ስለሆነባቸው ነው። ታዲያ ተረት ተረታቸውን የሚቀረጹ በሰው ርስት ላይ ተሁዋ አይደለም። በወረራ ገብተው ባለርስት ያደረገቻቸውን ኢትዮጵያ ትፍረስ ሲሉን ኦሮምያ የሚባለው በወረራ የተፈጠረ ኢምፓዬር ፈርሶ ርስቱ ለባለቤቶቹ፤ የአውራጃዎቹ ስም ወደ ጥንት መሠረቱ እንዲመለስ ትግል የማንጀምርበት ምድራዊ ምክንያት ሊኖር አይችልም።

# ከአሥራት ወልደየስ እንደበት

የቀዶ ሕክምና ሊቁ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ሲያቋቁም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ወክለው በጉባኤው ላይ ተሳትፈዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝብ ፊት የፖለቲካ ስብዕናቸው ጎልቶ የታየው በዚያን ዕለት በሰጡት አስተያየት ነው። በጉባዔው ውስጥ የታጨቁት ሁሉ ሃሳባቸው እንደ አንድ ሰው ነበር። ፕሮፌሰር አሥራት ብቻቸውን በልዩነት ነጥረው ወጡ። በአዳራሹ ውስጥ የሻዐቢያው ኢሳያስ አፈወርቂን በማየታቸው መደሰታቸውን ገለፁ። «አንድ ላይ ሆነን ስንታይ ልዩነት የሌለን ነን» ሲሉም አስረዱ። የኤርትራን የመገንጠል ጥያቄን በተመለከተ እዚያ አዳራሽ ውስጥ የተሰባሰቡት ጉባዔተኞች በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ኤርትራንም ሆነ ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል ማስገንጠል እንደማይችሉ አፅንኦት ሰጥተው መናገራቸውን ‹የአማራ ጉዳይ› የተባለው መፅሐፍ ያትታል። ይህ የፖለቲካ አቋማቸው ገናና ስም ከማስጠቱም በተጨማሪ ወደ ፓርቲ ፖለቲካ እንዲገቡ መንገድ የጠረገ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) መሪ ሆነው ብቅ ሲሉ በሕዝቡ ዘንድ የተደበላለቀ ስሜት መፍጠሩን መፅሐፉ ይጠቁማል።

አንዳንድ ሰዎች «ፕሮፌሰር አሥራትን ያስተማራቸው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኖ ሳለ እንዴት ለአማራ ብቻ ይታገላሉ?» «አሥራት ብሔርተኛ ናቸው እንዴ?» የሚል ጥያቄ አነሱ። ሁለተኛው ጥያቄ ‹የሕክምና ሊቁ እንዴት ወደ ፖለቲካ ገቡ?› የሚል ነው። በሕዝቡ ስሜት ውስጥ የሚንፀባረቁትን እነዚህን ጥያቄዎች አንስቶ የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን ጠይቋቸዋል። ከጥያቄዎች መካከል አንዱ «እንዴት የመአሕድ መሪ ሆነው ተመረጡ?» የሚል ነው።

ጋዜጠኛው ይህንን ጥያቄ ባቀረበላቸው ወቅት እስረኛ ሆነው ታመው ነበር። ቃለ መጠይቁን ያደረጉት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አልጋ ላይ እንደተኙ ነው። እንደ እሳቸው መልስ ከግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. በኋላ የአማራ ሕዝብ ላይ የተለያዩ ጥቃቶች ይሰነዘሩ ጀመር። አሥራት በራድዮ ጣቢያው ሲናገሩ ከሰማሁት ውስጥ ቃል በቃል ባይሆንም የማስታውሰው በሚል የሚከተለው እንደሆነ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ጸሐፊ ይገልፃሉ።

. . .ተገደሉ፣ ተፈናቀሉ የሚባሉ አማሮችን ሁኔታ በተደጋጋሚ እሰማለሁ። ይህ እንዴት ሊከሰት ቻለ እያልኩ ማሰቤ አልቀረም። ሰው



እንዴት አማራ ስለሆነ የጥቃት ኢላማ ይሆናል እያልኩ አስባለሁ። ይህንን ግድያና መፈናቀል ለማስቆምስ ምን መደረግ አለበት እያልኩ እንደ አንድ በእድሜና በትምህርትም ከፍ ብሎ እንደሚታይ ኢትዮጵያዊ መፍትሔውን አስብ ነበር። ታዲያ በዚህ መሀል አንድ ቀን የሚያውቁኝ ሰዎች ስብሰባ ጠሩኝ። ግብዣውን ተቀብየ ሄድኩ። የስብሰባው ዋና አላማ «ሰዎች አማራ ናቸው እየተባለ የከፍተኛ ስቃይ ሰለባ ሆነዋል፤ ይሄን እሳት እንዴት እናስቁመው? ሰው አማራ በመሆኑ መሰቃየት፣ መገደል የለበትም» የሚል ነው። ይህ ድምፅ ቤቱ ውስጥ በሰፊው ይንፀባረቅ ነበር። እኔም ይህንን ሃሳብ እደግፍ ነበር። ሰው የየትኛውም ብሔር አባል በመሆኑ መገደልም ሆነ መሰቃየት የለበትም የሚለው ፅኑ አቋሜ ነበር። ይህ መቆሚያ ያጣውን የአማሮችን ስቃይ ለማስቆም ድርጅት አቋቁመን ድምፃችንን እናሰማ፤ ሞትን፣ እንግልትን ለመከላከል ሰብሰብ ብለን በተደራጀ መልኩ የዜግነት ግዴታችንን እንወጣ የሚል ነበር። በወቅቱ እዚያ አዳራሽ ውስጥ አማሮች ብቻ አልነበሩም። ግድያው ያሳሰባቸው ሌሎች የሰው መብት ተቆርቋሪዎችም ነበሩ። በመጨረሻም የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) ተመሰረተ። ልብ አድርግ ምስረታው አማራ ናችሁ ተብለው ግፍ የሚፈፀምባቸውን ሰዎች ለመታደግ ነው። ሞትን ለማስቀረት ነው። እሳት ለማጥፋት ነው። ከዚያም ይህንን መአሕድን የሚመራ፤ የሚሰበስብ ሰው ይመረጥ ተባለ። ጥቆማ ተጀመረ። አንድ ሰው «አሥራት ወልደየስ» አለ። ሁሉም ጥቆማውን ደገፎ አጨበጨበ። እኔ ደግሞ ተነስቼ የራሴን አስተያየት ሰጠሁ። «እንዲህ አይነት ድርጅትን ለመምራት ከእኔ የተሻሉ ሰዎች አሉ» ብየ ተቃወምኩ። ነገር ግን «ይህ ድርጅት ዋና አላማው ሞትን ማስቆም ነው» አሉ። «አንተም በህክምና ሙያህ የምትሠራው ሞትንና ስቃይን ለመከላከል ነው። እንደ ህክምና ሥራህ ቁጠረው» በማለት ገፋፉኝ። «እውነት ለመናገር ምርጫውን የተቀበልኩት አማራ ስለሆንኩ አይደለም። ሞትን ስቃይን ለመከላከል ነው በማሰብ ነው እንጂ። . . . »

ለፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ የቀረበላቸው ሌላኛው ጥያቄ «እርስዎ የህክምና ሊቅ ሆነው ሳለ ወደ ማይታወቁበት ፖለቲካ እንዴት ገቡ?» የሚል ነበር። ምላሻቸው ይቀጥላል።

« . . . እኔ ፖለቲካ ውስጥ አልገባሁም። ምክንያቱም ፖለቲካ በዚች ሀገር የለም። ፖለቲካ ቢኖር ኖሮ እኔ አልገባም ነበር። ለፖለቲከኞች እለቅ ነበር። እኔ የገባሁት ሞትን፣ ስቃይን ለመከላከልና ለመቃወም ነው። የእሣት አደጋን ለመከላከል ነው የመአሕድ አባልና መሪ የሆንኩት። ፖለቲካ ቢኖር ኖሮ ሰው አይገደልም። ሰው አይሰቃይም ነበር። ፖለቲካ ቢኖር ኖሮ በሰከነ መንፈስ ሁሉም ነገር በውይይት፣ በመግባባት፣ በሃሳብ ክርክር በድምፅ ብልጫ እና በግልፅነት ይካሄድ ነበር። ፖለቲካ ስለሌለ ግድያና እንግልት በዛ። እኔም መአሕድን የተቀላቀልኩት ፖለቲካው እስከሚመጣ ነው። የዚያን ጊዜ የመአሕድ መሪነቱን ለፖለቲከኞች እለቃለሁ። . . . »

ስለ አማራ ብሔርተኝነታቸው የተጠየቁት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደደየስ «በወቅቱ ልክ እንደ አማራ በማንነቱ ለአደጋ የተጋለጠ ብሔር ቢኖር ኖሮ ለእርሱም በተመሳሳይ መልኩ እቆምለት ነበር» ሲሉ አብራርተዋል።

ፕሪፌሰር አሥራት ወልደየስና ፓርቲያቸው የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት በዚህ ሁኔታ አያሌ ሥራዎችን ሰርተዋል። ከኢሕአፓ የተገነጠሉ ፖለቲከኞች ኢሕዴን በሚል ስያሜ ከገዥው ፓርቲ ጋር በመሆን ከአማራው ሕዝብ ሳይወለዱ ወይም አማራዊ ስነ ልቦና ሳይኖራቸው በኢሕአዴግ የብሔር ፖለቲካ ውስጥ አማራን እንዲወክሉ ተደርገው ቆይተዋል። የመአሕድ መወለድ በፈጠረው ድንጋጤ ይህ ፓርቲ ግብሩ ያው ቢሆንም ቢያንስ ስሙን የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ወደ ሚል ተቀይሯል። መአሕድ ዛሬ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሚሰጣቸው ፖለቲከኞች የወጡበት ቤትም ነው።



ምዕራፍ ይመር

# የታገቱ ተማሪዎችና መንግሥታዊ ክህደቶች

የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከታገቱ በርካታ ቀናት ተቆጠሩ። ተማሪዎቹ እምጥ ይግቡ ስምጥ የሚናገር ባለሥልጣን ግን ከቶም አልተገኘም። ከሞያሌ እስከ ደዋኔ፣ ከሞጣ እስከ ነፋስ መውጫ ድረስ፣ ሃገርን 'አስተዳድራለሁ' የሚለው መንግሥት፣ የዜጎችን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታውን ረስቶ፣ የተማሪዎቹ ቤተሰቦችን ጭንቀት ከቁብ ላለመቁጠር ሰበብ እየደረደረ ነው። እንዲያውም ሃሰተኛ መረጃ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የተናገሩ ባለሥልጣናት ሲሾሙ አይተናል፤ እያየንም ነው። አቶ ንጉሱ ጥላሁን ስለተማሪዎቹ የተምታታ መረጃ ከሰጡ በኋላ፣ የአንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሓላፊ ሆኖ ተሹመዋል። በሠሩት አስከፊ የማለባበስ ሥራ ሲቀጡ አላየንም። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ጭምር ተማሪዎቹ ያሉበትን ቦታ 'እግዜር ይወቀው' ከማለት አንስቶ፣ 'ራሳቸው ብቅ ይሉ ይሆናል' እስከማለት ድረስ በብዙ ቤተሰቦች ቁስል ላይ ጨው ሞጅረዋል። የፌዴራል ፖሊሱ አጋፋሪ እንደሻው ጣሰውም አንዳች መረጃ ላለመስጠት ቃል የገቡ ይመስላል:: የበታች ሹሙ፣ የህዝብ ግንኙነት ሓላፊው ጄይላን አብዲ እንዲሁ ፍንጭ ላለመናገር ዳር - ዳር በማለት ሲዞሩ ታዝበናል። መንግሥት እና ተከፋይ ምንደኞቹ ያቀናበሩት፣ 'ከታጋች ተማሪዎች መካከል፣ ሁለቱ አምልጠው ወጡ' የሚለው ዜና፤ ስርዓቱ ምን ያህል ድክመቱን በውሸት ለመሸፈን እንደሚጥር አሳይቶናል። ብዙ መንግሥታዊ ቅሌቶችን በተማሪዎቹ እገታ ሰሞን አስተውለናል።

## መታገታቸው ከተነገረ በኋላ ደብዛቸው የጠፋው ተማሪዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

| ተ.ቁ | ሙሉ ሥም | በዶምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ - የትምህርት ክፍል | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|
| 1 | በላይነሽ መኮንን ደምለው | የእርሻ ምጣኔ ሃብት | 1ኛ ዓመት |
| 2 | ሳምራዊት ቀሬ አስረስ | ጋዜጠኝነት | 2ኛ ዓመት |
| 3 | ዘውዴ ግርማ ፈጠነ | የእርሻ ምጣኔ ሃብት | ተመራቂ |
| 4 | ሙሉ ዘውዴ አዳነ | የማሕበረሰብ ሳይንስ ጥናት | 2ኛ ዓመት |
| 5 | ግርማቸው የኔነህ አዱኛ | ባዮቴክኖሎጂ | ተመራቂ |
| 6 | ስርጉት ጌጤ ጥበቡ | የተፈጥሮ ሳይንስ | 1ኛ ዓመት |
| 7 | ትዕግስት መሳይ መዝገቡ | ቅድመ ዩኒቨርሲቲ | 12ኛ ክፍል (የአካባቢው ነዋሪ) |
| 8 | መሰረት ከፍያለው ሞላ | የተፈጥሮ ሳይንስ | ተመራቂ |
| 9 | ዘመድ ብርሃን ደሴ | የተፈጥሮ ሳይንስ | ተመራቂ |
| 10 | ሞነሞን በላይ አበበ | ጋዜጠኝነት | 2ኛ ዓመት |
| 11 | ጤናዓለም ሙላቴ ከበደ | የእርሻ ምጣኔ ሃብት | 2ኛ ዓመት |
| 12 | እስካለሁ ቸኮል ተገኝ | ኬሚስትሪ | ተመራቂ |
| 13 | አሳቤ አየለ አለም | የዕፅዋት ሳይንስ | ተመራቂ |
| 14 | ቢተወኝ አጥናፉ አለሙ | ኮምፒዩተር ሳይንስ | ተመራቂ |
| 15 | ግርማው ሀብቴ እማኛው | ሜካኒካዊ ምህንድስና | 3ኛ ዓመት |
| 16 | አታለለኝ ጌትነት ደረሰ | የተፈጥሮ ሳይንስ | 1ኛ ዓመት |
| 17 | ክንድዬ ሞላ ገበየሁ | የተፈጥሮ ሳይንስ | 1ኛ ዓመት |



መንግሥት የዜጎችን ሰላምና ደህንነት የማስከበር ሓላፊነቱ አጠያያቂ አይደለም:: በተለይ ደግሞ እራሱ ባቋቋመውና ራሱ በሚመራው ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከወላጆቻቸው በአደራ የተረከባቸውን ተማሪዎች ደህንነት የማስጠበቅ ታላቅ ግዴታ አለበት:: በሕዝብ ሳይመረጡ ሥልጣን የያዙት ዶ/ር አብይ አሕመድ እና መንግሥታቸው የዜጎችን ደህንነት ካለማስጠበቃቸውም በላይ በተደጋጋሚ እያካሄዱ ላሉት መንግሥታዊ ቅጥፈት በሕግ ሊጠየቁ ይገባል::

ይህንን ለማድረግ እና ወደፊትም ተጠያቂነት የሰፈነበት ስርዓተ መንግሥት ለመገንባት የምሁራን ሚና ከፍተኛ ነው:: በተለይም በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ምሁራን፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ የሕግ ባለሙያዎች ጉዳዩን ለዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ገዢው ፓርቲና መንግሥት ሁልጊዜም የሚያስቀድሙት ፖለቲካዊ ትርፋቸውን በመሆኑ እነኚህ ገለልተኛ ምሁራን፣ ባለሙያዎችና አደረጃጀቶች መንግሥትን የመግራት ሀገራዊ ሓላፊነት አለባቸው:: ምሁራኑ በዓባይ ግድብ ግንባታ ላይ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን አሳልፋ እንዳትሰጥ እንዳደረጉት ርብርብ ሁሉ፣ የታገቱ ተማሪዎችን ጉዳይም ለተለያዩ ዓለማቀፍ ተቋማት ቢያሳውቁና ክትትል ቢያደርጉ መልካም ይሆናል:: አንዳንዶች ከጀቦናቸው የፍርሃትና የአድርባይነት ገሳ ሊወጡ ይገባል::

በአጠቃላይ የተማሪዎቹ ጉዳይ የተረሳ ይመስላል። በመንግሥታዊ ተዋፅኦ ውስጥም እንዳይነገር ጥብቅ ትዕዛዝ እንደተላለፈ ለመገመት አይከብድም። ነገር ግን ሌት ተቀን የሚያነቡና የሚጨነቁ ወላጆች ዘንድ ህመሙ አልሻረም። ስለእነዚህ ወገኖች 'ያገባናል' ያሉ ዜጎችም ተሰባስበው እየተንቀሳቀሱ ነው፤ መንግሥታዊ ጫና ቢኖርባቸውም። በመሆኑም የእነዚህ ታጋች ተማሪዎች መጨረሻ እስኪታወቅ ድረስ፣ በመንግሥት የተድበሰበሱ ወሬዎች ሳንዘናጋ መጠየቅ፤ መታገል፣ እሪ ብሎ መጮህ፣ . . . ይኖርብናል።

## ሚዛኑ ይመዘን

ሚዛኑ ሲዋልል
ባለው እያሻማ በሌለው ሲያመልል
ዳኑ መሃል ሆኖ ምሰሶው ሲገለል፡፡
ከስፍራው ተገሶ
ከነፈሰው ነፍሶ
ያልበላውን አኮ
ሰምበሌጡን ታኮ
ቀኙን እየጣለ ግራውን ካነሳ
ገለባውን አዝሎ ፍሬውን ከረሳ
ፍትህን አዛብቶ ካሳየን አበሳ
የሩቁን አስታውሶ የቅርቡን ከረሳ
በጥጉ አማሎ መሃሉን ከበሳ
ምን ቀረን ላሁኑ
ምን ቀረን ለመጪው
በምስቅልቅሎሹ በውጥንቅጥ ዓለም
መስፈርቱን ከመስፈር ፍቱን መፍቴ የለም፡፡

(በቃሉ ሰው መሆን)



## ታለቁ እስክንድር!!!

ምን አለ የጎደለው ምንስ አለ ያጣው?
አደባባይ ወጥቶ ተሚጋች ያረገው?
አልኩኝ እኔ አስቤ ይሄ ሰው ምንድን ነው?
አያገባው ገብቶ አይሆኑ እሚሆነው?

ይህ የጅል አሳቤ እኔኑ አሳቀኝ፣
በእሱ ሰውነት ውስጥ የኔ ሲቀልጥ ታየኝ፤
እሱማ ሰውዬው የሰው ልክ ከፍታ፣
ፍትህ ከሀገር ጠፍቶ ሰዉ ሲንገላታ፣
ለምን? ብሎ የቆመ ከራሱ ደስታ፣
የሌላው ቢያመው ነው እረፍት ቢያጣ ፋታ፣
ለብዕር መሳሪያው ሳይመርጥለት ቦታ፣
በሁለም ሥፍራ ላይ ያተመው የወገን መከታ፣
መሆኑን ሲያሳይ ነው ከቶም ላይረታ፣
ጉዳዩም ያልሆነው ቢታሰር ቢፈታ፤

እስክንድር ሀገሬን በአቻ ልክ አቁመን፣
ከቢጤዋ ተርታ ፍጹም አለካከተን፣
አንተኛም አናርፍም  ሳናይ ትንሣኤዋን፣
ይላል በብዕሩ አድምቆ እየጻፈ፣
ትናንት ሆነ ዛሬ ከዚህ አላለፈ፣
መሳሪያው ይኸው ነው ሌላን አልገደፈ፡፡

ጦርን አልጨበጠ ደጋን አልወጠረ፣
አስወንጭፎ በአካል አንዲትም አልጫረ፣
ብዕሩ ነው ጦሩ ቃል እየመነዘረ፣
እውነትን መስካሪው ልክን የገበረ፣
ዋሾን አስለፍልፎ ከደጅ ያሳደረ፡፡



ርብቃ አብርሐም
-ከአውስትራሊያ



ኢትዮጵያ ዳግም
የህሊና እስረኞች
ቤት እንድትሆን
መፍቀድ የለብንም!
ባልደራስ
ለእውነተኛ ዲሞክራሲ